# አዲስ ዘመን

እናድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 281 ሰኔ 11 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# አዲሱ"ዓባይ ፪" መርከብ

## በነዳጅ ጫኝ መርከቦቻችን ሲደርስብን የነበረውን ኪሳራ ማስቀረት ያስቻለ ነው

### - በቀን 11 ሺህ ዶላር ገቢ ያስገኛል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ “ዓባይ ፪” መርከብ በሁለቱ ነዳጅ ጫኝ መርከቦቹ ሲደርስ የነበረውን ኪሳራ ማስቀረት እንደሚያስችል የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አስታወቀ፡፡ በቀን አስራ አንድ ሺህ ዶላር የተጣራ ትርፍ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ ደምሰው በንቲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲሱ”ዓባይ


አዲሱ “ዓባይ ፪” ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










## ዩኒቨርሲቲው በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ

### ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናትና ምርምሮችን እያካሄደ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ላይ መሆኑን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ፡፡

የዩኒቨርሲቲው የጥናት፣ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ምትኬ ሞላ እንደተናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲው የዘላቂ የልማት ግቦች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ረገድ ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በዘላቂ የልማት ግቦች ድህነትን ማጥፋት፣ የተሻሻለ የጤና ሥርዓት መዘርጋት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ መገንባት፣ የቱሪዝም ሀብቶችን በተቀናጀ መንገድ ለሃገር ዕድገት ማዋልና በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናቶችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ለሚያከናውናቸው የምርምር ሥራዎች በጀት ከመመደቡ በፊት የጥናቱ ትኩረት በዘላቂ የልማት


ዩኒቨርሲቲው በዘላቂ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፕሮፌሰር ምትኬ ሞላ


ዶክተር ተስፋዬ ዘለቀ

## በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዙሪያ እየተካሄደ ያለው ሀገራዊ ውይይት በሐምሌ ወር ይጠናቀቃል

### -ውይይቱ በሁሉም ክልሎች ይካሄዳል

### -መስከረም ላይ ያለቀለት የፖሊሲ ሰነድ ለሕዝብ ይቀርባል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዙሪያ እየተካሄደ ያለው ግብዓትን የማሰባሰብ ሃገራዊ ውይይት እስከ መጪው ሐምሌ ወር 2015ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የፍትህ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ውይይቱ በሁሉም


በሽግግር ፍትህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አወል ሱልጣን

## የመጪው ትውልድ እምቅ አቅም የታየበት የፈጠራ ሥራ

**ማህሌት ብዙነህ**

ለአንድ ሀገር ዘላቂ እድገት በዓለም አቀፍ ደረጃ በዕውቀትና በክህሎት ተወዳዳሪ የሆነ ትውልድ መፍጠር ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ለታዳጊዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ዘመኑ በዋጀ እውቀት፣ቴክኖሎጂ፣ ፈጠራና ክህሎት መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

ሰሞኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት


የመጪው ትውልድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ዜና




# ለማዕከሉ የተደረገው ድጋፍ ማኅበራዊ ሚዲያን ለበጎ ነገር የመጠቀም ተምሳሌት ነው

## - ከሰባት ሺህ በላይ ሕፃናት የልብ ቀዶ ህክምና ለማግኘት ይጠባበቃሉ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ለልብ ህሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል የተደረገው 50 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የህክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ ማኅበራዊ ሚዲያን ለበጎ ነገር የመጠቀም ተምሳሌት መሆኑን የማዕከሉ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ህሩይ አሊ ገለጹ፡፡

ለኢትዮጵያ ልብ ህሙማን ህጻናት መርጃ ማዕከል የተበረከተውን ድጋፍ ሲቀበሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደገለጹት፤ በጋዜጠኛ ህይወት ታደሰ ለማዕከሉ የተደረገው የህክምና ቁሳቁስ ድጋፍ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ ይህ ድጋፍ በመደረጉም ምስጋናችን የላቀ ነው ብለዋል፡፡

የተደረገው ድጋፍ ለሥራችን ትልቅ እገዛ ያደርጋል ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ድጋፉ ማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ ነገር ለመጠቀም ተምሳሌት መሆን የሚችል ሥራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በድጋፍ መርሃ ግብሩ ላይ ጋዜጠኛ ህይወት ታደሰን ወክላ ንግግር ያደረገችው ጋዜጠኛ የኋላሸት ዘሪሁን፤ ጋዜጠኛ ህይወት ታደሰ ነዋሪነቷ በሰሜን አሜሪካ መሆኑን ጠቅሳ፤ ከአራት ዓመታት ወዲህ “ማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ አላማ” በሚል መሪ ቃል ድጋፍ እያሰባሰበች መሆኑን ተናግራለች፡፡ በዚህም ለኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ህፃናት መርጃ ገቢ በማሰባሰብ በተለያዩ ጊዜያት ህፃናቱን ስታሳክም መቆየቷን ገልፃለች፡፡

የልብ ቀዶ ህክምና እና የደም ስር ውስጥ ህክምና መድኃኒቶቹ በአይነታቸው ዘርፈ ብዙ እና ዋጋቸውም ከፍተኛ ስለሆነ ጥሬ ገንዘብ ቢኖር እንኳን በሀገራችን ውስጥ እንደልብ ማግኘት ከባድ ነው ያለችው ጋዜጠኛዋ፤ በመሆኑም ግምቱ ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የህክምና ቁሳቁስ ለማዕከሉ ማበርከት ችለናል ብላለች፡፡

ማዕከሉ እስከዛሬ ከሦስት ሺህ በላይ ህጻናት እንዲታከሙ ሲያደርግ ያለምንም ክፍያ ከተለያዩ ልበ ቀና ከሆኑ ግለሰቦች እና ሀገር በቀል እንዲሁም ከሀገር ውጪ ባሉ ድርጅቶች በሚደረገው ርዳታ ነው ያለችው ጋዜጠኛ የኋላሸት፤ ማዕከሉ ከሀገሪቱ በጠቅላላ የሚላኩ ታካሚዎችን የሚያስተናግድ በመሆኑ በአሁኑ ሰአት ከሰባት ሺህ በላይ ሕፃናት ቀዶ ህክምና የሚጠባበቁ መሆናቸውን አስገንዝባለች፡፡ በመሆኑም ድጋፍ የሚያስፈልገው ተቋም ነው ብላለች፡፡

ማዕከሉ በጋዜጠኛ ህይወት ታደሰ ከተመሰረተው ‘ላይፍ ፎር አፍሪካ’ የተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በዘላቂነት አብሮ ለመስራትም የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል፡፡

# በኢፕድ ስልጠና ማዕከል ያገኙት ስልጠና በሥራቸው ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ሰልጣኞች ገለጹ

**ሳሙኤል ወንደሰንና በቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በኢፕድ ስልጠና ማዕከል ያገኙት ስልጠና በሥራቸው ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ሰልጣኞች ገለጹ። የኢፕድ ስልጠና ማዕከል ለአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ድርጅትና ለንግድ ቢሮ አመራሮች እና ሠራተኞች ስልጠና ሰጥቷል።

ማዕከሉ ለአዲስ አበባ አውቶቡስ ድርጅት አመራሮችና ሰራተኞች "መልካም ስብዕና ግንባታ ለአገልጋይነት አስተሳሰብና ተግባር" በሚል ጽንሰ ሃሳብ ከሰባት ሺህ በላይ ለሚሆኑ አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና እየሰጠ ይገኛል። የሚሰጠው ስልጠና በአምስት ዙር የሚከናወን ሲሆን፤ በትናንትናው እለት ከ800 በላይ ለሆኑ የድርጅቱ አመራሮች እና ሰራተኞች የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛው አለሙ በስልጠናው መክፈቻ እንደተናገሩት፤ “ድርጅታችን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎችን በቀን ያገለግላል። ይህም ማለት የድርጅቱ ሠራተኞች በቀን ከበርካታ ሰዎች ጋር ተግባቦት ያደርጋሉ።

የተገልጋይን አመለካከት በመገንዘብ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል። ይህንንም ይበልጥ ለማጠናከር ኢፕድ ስልጠና እንዲሰጠን ወስነናል ብለዋል።

ኢፕድ አንጋፋና ትልቅ የሚዲያ ተቋም ሲሆን፤ በስልጠና ዙሪያም በቂ ልምድ ያለው ተቋም ነው። ለዚህም አውቶቡስ ድርጅቱ ከሰባት ሺህ በላይ አመራሮች እና ሰራተኞችን በኢፕድ ስልጠና ማዕከል ለአምስት ቀናት ማሰልጠን ጀምሯል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ የሚሰጠው ስልጠና በሥራቸው ላይ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ ኢፕድ ከአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ድርጅት ጋር በጋራ በመስራቱ መደሰታቸውን ገልጸው፤ ኢፕድ "መልካም ስብዕና ግንባታ ለአገልጋይነት አስተሳሰብና ተግባር" በሚል ጽንሰ ሀሳብ የሚሰጠው ስልጠና ከድርጅቱ የእለት ተዕለት ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ፋይዳው ላቅ ያለ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኢፕድ በአዲስ አበባ የአውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ሁኔታ የሚያሳዩ ታሪካዊ ፎቶዎች፣ ዜናዎች እና በርካታ ጽሑፎች ዶክመንት አድርጎ መያዙን ጠቁመው፤ ይህንን የድርጅቱን ታሪክ በፎቶ ቡክ፣ በመጽሔት እና በዶክመንተሪ ለመያዝ በሚፈልግበት ወቅት ኢፕድ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ ዜና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጠና ማዕከል “አገልጋይ ስብዕና ለውጤት” በሚል መሪ ሀሳብ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል።

በስልጠና መርሃ ግብሩ ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የህይወት ክህሎት አሰልጣኝ የሆኑት ዶክተር አሸናፊ አበራ እንደተናገሩት፤ ለሀገርና ለህዝብ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት አመራር ወይም ሰራተኛ ከመሆን በፊት ሰው መሆን ይቀድማል።

ሰው በግል ህይወቱ መልካም፣ ለራሱ የሚጠነቀቅና ዓላማ ያለው ሲሆን የሚያገለግልበትን ተቋም ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት ትልቅ ሚና እንዳለው ገልጸው፤አነቃቂ ስልጠናዎች መሰጠታቸው ተቋማት ከሀገርና ከህዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለማሳካት ጠቃሚ መሆኑን አውስተዋል።

ሰራተኛው እርስ በራሱና ከአመራሩ ጋር የተሻለ የስራ ቀረቤታ በመፍጠር ለተቋም ዓላማ መሳካት የጋራ አስተሳሰብ ኖሮት ደካማ ጎን ላይ ከማተኮር ይልቅ ጠንካራ ጎኖችን በማጉላት ሚዛናዊ ሆኖ መስራት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

በሰልጣኞቹ በኩል ለመለወጥ ትልቅ ተነሳሽነት እንደነበረ የጠቆሙት ዶክተር አሸናፊ፤ የኢፕድ የስልጠና ማዕከል ያሳየውን መልካም ጅማሮ በተደራጀ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል።

የቢሮው የሰው ሀብት ልማትና ስራ አመራር ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ሚኤሳ እንደጠቆሙት፤ በግልም ሆነ በስራ ህይወት ለመቀየር የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል።

የአገልጋይነት መንፈስን በመላበስ ሰራተኛው ከራሱ በፊት ህዝብን ሊያገለግል ይገባል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች የሚኖራቸውን ግንኙነት ይበልጥ ለማሻሻል ስልጠናው ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢፕድ የስልጠና ማዕከል ያቀረበልን አሰልጣኞች ብቁ እና በዘርፉ ልምድ ያላቸው በመሆናቸው ስልጠናው ከዚህ በፊት ከሚሰጡ ስልጠናዎች በአሳታፊነቱ የተለየ መሆኑን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

ስልጠናውን በመከታተል ላይ የሚገኙት አቶ ተሰማ ጨመዳ በበኩላቸው፣ ስልጠናው ሁሉን አቀፍና ሰራተኛው ስለተለያዩ ጉዳዮች ቀና አስተሳሰብ እንዲኖረውና በስራውና በግል ህይወቱ ላይ ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ስልጠናው አሳታፊና ለስራቸው ትልቅ ተነሳሽነት እንደፈጠረላቸው የገለጹት ወይዘሮ ጽጌ ኪዳነ፤ ሌሎች በግልም ሆነ በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች እንዲህ አይነት ስልጠናዎችን ቢያገኙ ለስራቸው መሳካት ትልቅ ጥቅም አለው ነው ያሉት።

ወይዘሮ ሄለን እሸቱ በበኩላቸው፤ ስልጠናው ወቅቱን የጠበቀና በተቋማቸው አገልግሎት ፈልገው ለሚመጡ ባለጉዳዮች የአገልጋይነትን መንፈስ በመላበስ እንዲሰሩ እንዳነሳሳቸው አውስተዋል።

የኢፕድ ስልጠና ማዕከል ሰሞኑን ለተከታታይ ቀናት ለአስር ተቋማት በ14 ርዕሶች ጉዳዮች ላይ ለፌዴራልና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠናዎች እየሰጠ መሆኑ ይታወቃል።

# “የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ዛሬ በህጻናት ላይ የምንሰራው ሥራ ወሳኝነት አለው”

## -የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ ፡- የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ዛሬ በህጻናት ላይ የምንሰጠው ትኩረትና የምንሰራው ሥራ ወሳኝነት አለው ሲል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር "ሰላም ፣ፍቅር እንክብካቤና ጥበቃ ለሁሉም ህፃናት" በሚል መሪ ቃል በአፍሪካ ለ33ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ32ኛ ጊዜ የሚከበረውን የአፍሪካ ህፃናት ቀንን አስመልክቶ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር በትናንትናው እለት በእንጦጦ ፓርክ ተካሂዷል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በመርሀ-ግብሩ ላይ እንደገለፁት፤ "ነገን ዛሬ እንትከል" በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በአፍሪካ የህፃናት ቀን መከበሩ ለነገ ሃገር ተረካቢ ለሆኑ ህፃናት ዛሬ የምንሰጠው ትኩረትና የምንሰራው ስራ ነገ የተሻለች ሃገር ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑ ማሳያ ነው።

በአፍሪካ የህፃናት ቀን የተካሄደው የችግኝ ተከላ መርሀ-ግብር በሀገሪቱ በተደጋጋሚ በሚከሰት ድርቅ፣ በጦርነትና በተለያዩ ችግሮች የተፈናቀሉና በመካከላችን ያልተገኙ ህጻናትን የምናስበበትና የምንደጋገፍበት እንዲሆን ያለመ ነው ሲሉ ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ተናግረዋል ።

ይህ የአረንጋዴ አሻራን የማኖር መርሀ ግብር ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን 25 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል። በቀጣይ ሃገርን ተረካቢ ህጻናት በመሆናቸው ዛሬ የምናደርገው ተግባር ለነገ ትልቅ አሻራ ነው። ለዚህም ህጻናት ዕድገት ላይ በማተኮር እና በማካተት እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለብን ብለዋል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የሴቶችና ህፃናት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ በበኩላቸው ፤ ዛሬ ላይ የሚሰራው ስራ ለነገ ሀገር ግንባታ ትልቅ ድርሻ አለው ፤ በዚህ መርሀ ግብር ላይ ህጻናትን በማሳተፍ ህጻናት ሀገራቸውን አውቀው እንዲያድጉ እና ሀገር ተረካቢ የመሆናቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለማድረግ ይረዳል። መንግስት በህጻናት ተሳትፎ ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው ብለዋል።

ችግኝ መትከል እና ህጻናት ላይ መስራት ተመሳሳይ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህፃናት ማኅበራዊ ጉዳይ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ህይወት ጉግሳ ፤ ሰላማዊ ፣ውጤታማ እና ታላቅ የሆነች ሃገር ለመገንባት ከተፈለገ ህጻናት ላይ መስራት ግድ ይላል ብለዋል።

በመርሀ ግብሩ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ፣የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የሴቶችና ህፃናት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ እንዲሁም የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህፃናት ማህበራዊ ቢሮ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች፣የህጻናት ፓርላማ አባላት እንዲሁም ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተወጣጡ ተማሪዎች በመገኘት አሻራቸውን አሳርፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በኮንትሮባንድ ላይ እየተደረገ ያለው ቁጥጥር ይጥበቅ!

በኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች የሚካሄዱ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዱ ይገኛሉ። የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱን ኢንዱስትሪ አልባ እስከ ማድረግ አቅም እንዳላቸው በተደጋጋሚ ይነገራል። ይሁን እንጂ ከገቢና ወጪ ንግድ ጋር የተያዘው ሕገወጥ ንግድ ዛሬም በኢትዮጵያ አሳሳቢነቱ እንደጎላ ነው።

በገቢ ምርቶች ረገድ አብዛኞቹ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር እንደሚገቡ መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህም ሳቢያ የሀገር ውስጥ አምራቾች እየተጎዱ እንደሚገኙ ሳይጠቀስ ታልፎ አያውቅም። ሕገወጥ ንግድ የተለያዩ መገለጫዎች ያሉት እንደመሆኑ ኢትዮጵያ በሕገወጥ መንገድ በሚደረጉ ንግዶችና በገንዘብ ዝውውር ያጣችው የሀብት መጠን ከዓመት ዓመት እያደገ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በአምስት ዓመታት ውስጥ ብቻ 70 ቢሊዮን ዶላር በደረሰኝ ማጭበርበር እንደምታጣ የሚያመላክቱ ጥናቶች ለችግሩ ግዝፈት ማስረጃ ናቸው። ይህም ከገቢና ወጪ ንግድ ሒደት ጋር ተያይዞ ዋጋን አሳንሶና ከፍ አድርጎ በማቅረብ በሚፈጸም ማጭበርበርና ገንዘብን በሕገወጥ መንገድ ከሀገር በማሸሽ (በካፒታል ፍላይት) የሚታጣ ነው። እዚህ ላይ የበይነመረብ ግብይትን በመጠቀም መንግሥት የማያውቃቸው ንግዶች እንደሚኖሩ መጠርጠሩም አይከፋም። እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ተደማምረው በአሁኑ ወቅት የሕገወጥ ንግዱ በህጋዊ መንገድ የሚካሄደውን እየተፈታተነ መሆኑ ችግሩን አንገብጋቢ አድርጎታል።

በኮንትሮባንድ የሚገባውና የሚወጣው ብዛት ያለው ሲሆን በአንፃሩ ተያዘ የሚባለው ግን አነስተኛ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ለዚህ ደግሞ የተቀናጀ አሰራር አለመኖር፣ የችግር ፈጣሪዎቹ ተለዋዋጭ ባህሪ ችግሩ እልባት እንዳያገኝና ሁሌም አሳሳቢ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ። የኮንትሮባንድ ቁጥጥሩ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ካልተሳተፈበት ውጤታማ እንደማይሆን ሁሉም የሚገነዘበው ሃቅ ነው። ኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ አልባ ሊያደርጋት የሚችለው ትልቁ ሥጋት ኮንትሮባንድ ነው። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ በሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር መወዳደር አቅቷቸው እንዲዘጉ እስከማድረስ የሚዘልቅ ትልቅ አደጋ አለው።

ኮንትሮባንድ ከኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችና ከመሳሰሉት አልፎ ወሳኝ የሚባሉ መድኃኒቶች ሳይቀር በሕገወጥ መንገድ እየገቡ መሆኑ ችግሩን ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ቀውስ የሚፈጥር ያደርገዋል።

ይህ አሳሳቢ ችግር በጊዜ መላ ካልተበጀለት በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆኖ የሚያመርተው የሀገር ውስጥ አምራች በኮንትሮባንድ በሚገባውና በተሻለ ጥራትና በዝቅተኛ ዋጋ መሃል ከተማ ላይ እየተሸጠ በሚገኘው ምርት እየተንኮታኮተ መሄዱ አይቀሬ ነው። የሀገር ውስጥ አምራች ጉዳት ውስጥ እየወደቀ ከሄደ ደግሞ በሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ የሚያርፈው በትር ቀላል አይሆንም። በዚህ ሂደትም መንግሥት ከፍተኛ የሚባል የታክስ ገቢ እያጣ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

የሕገወጥ ንግዱ መነሻ ሞራል የጎደላቸው ነጋዴዎች በምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የሚፈጥሩት ሰው ሠራሽ የሆነ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው። እነዚህ ነጋዴዎች ሕጋዊ ነጋዴዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። በአንድ አካባቢ የፍላጎትና የአቅርቦት አለመመጣጠን እንዲፈጠር አድርገው በሌላ በኩል አቅርቦቶችን ለማሟላት በኮንትሮባንድ ንግድ ውስጥ በመሳተፍ የተሻለ ጥቅም የሚያገኙበት ሁኔታ ሊፈጥሩ እንደሚችሉም መገንዘብ አዳጋች አይደለም።

በዚህ ውስጥም የሙሰኛ ተዋናዮች ተሳትፎ፣ ድጋፍና ሽፋን መስጠት ችግሩን እያባባሰው ነው። በፈቃድ አሰጣጥ ላይ፣ በድንበር ጥበቃ ላይ፣ በግብር አከፋፈልና የመሳሰሉት ላይ የሚታየውን ችግር የሚፈጥሩትም እነዚሁ አካላት ናቸው።

ለሕገወጥ ንግድ መስፋፋት በዋነኛነት የሚጠቀሰው በድንበሮች አካባቢ ያለው የሳሳ የቁጥጥር ስርአት ነው። በዋናነት ግን ችግሩን በቋሚነት ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መፍጠርና ከዘመቻ ይልቅ መልክ ቋሚና ዘላቂ አሰራር መዘርጋት ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረጉ ተጨባጭ ለውጥ እንዲታይ ያደርጋል። ለዚህ ደግሞ አንዱ የመፍትሔ ቁልፍ የመንግሥት ቁርጠኝነት ነው:: ሙስና ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ንግድ የተቆራኙ በመሆናቸው ይህን መዋጋት ቅድሚያ ሊሰጠው ግድ ነው።

ኢንሳና ቴሌኮሙዩኒኬሽንን የመሳሰሉ ተቋማትን በመጠቀም የቁጥጥር ሥራን በዘመናዊና በተቀናጀ መልኩ መሥራት አስፈላጊ ነው:: ሕገወጥ የገንዘብና እያንዳንዱ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥም ይሁን የውጭ አጋር ስላለው ይህንን ያመቻቸው ማነው ብሎ መመርመርና በተጨባጭ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ተገቢውን ርምጃ መውሰድ ይገባል::

አንድ የኮንትሮባንድ ዕቃ ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ እንዲሁም አልፎ ሲመጣ ያሳለፈን ኬላ ተጠያቂ የሚያደርግ ጠበቅ ያለ ሥርዓት መዘርጋትም ችግሩን ሊያቃልል ይችላልና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ይህንን የህጋ ጣለት የሆነ ተግባር ለማስቆም ሊረባረብ ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## አገራዊ ምክክሩ የዘላቂ ሰላማችን ምንጭ እንዲሆን

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ አያሌ ለውጦችን አስተናግዳለች። በዚህ ጥቂት ጊዜ ውስጥ "የደፈረሰው ሲጠራ፣ የጠራው ሲደፈርስ" ተመልክተናል። በውይይትና በስምምነት የፈታናቸው አገራዊ ሸንቁሮች ያሉትን ያህል ወደ አላስፈላጊ ግጭቶች፣ ጥፋቶችና መቃቃሮች ውስጥ የከተቱንም በርካታ ጉዳዮች በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ተመልክተናል። በጥቅሉ ተደማምጠንም፤ ሆድና ጀርባ ሆነንም እነዚህን ጊዜያት አልፈን ዛሬ ላይ ደርሰናል። ከሁለቱም ክስተቶች ትምህርቶችን መውሰዳችንም አልቀረም።

ሰክነን በመወያየታችን የፖለቲካ ልዩነቶቻቸውንና ፓርቲዎቻቸውን ወደጎን ትተው ለአገር እድገትና ለህብረተሰብ ልማት በጋራ መንግሥት በሚለው ጥላ ስር የተሰባሰቡ የኢትዮጵያ ምሁራንን አፍርተናል። ለዚህ ሁነኛ ማሳያው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ካቢኔና በተዋረድ ባሉ የሥራ ሃላፊነት ቦታዎች የሚሰሩ ፖለቲከኞች ናቸው።

በተቃራኒው ገመድ በመጓተታችን፣ ቃታ በመሳባችን የሃሳብ ልዩነቶችን በንግግር ለመፍታት ባለመቻላችን ምክንያት ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ ዜጎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ የአገር ኢኮኖሚ እንዲደቀቅና በግሽበት ተፅእኖ ውስጥ እንዲይ ሆነናል። እነዚህ ሁለት ተቃራኒ መንገዶች ለቀጣይ ውሳኔያችን፣ ለአብሮነታችን እና ለትውልድ አስረክበን ለምናልፋት አገራችን ትልቅ ትምህርት የተውልን ክስተቶች ናቸው።

ዛሬ ላይ ያሳለፍናቸውን የለውጥና የነውጥ ጊዜያት የምንገመግምበት እና የተቀመጡ አማራጮችን በስክነት መርጠን መደላድል የምንፈጥርበት ነው። ኢትዮጵያ በፖለቲካ ልዩነት በተፈጠረ የሰሜኑ ጦርነት በቆየችባቸው ጊዜያት ከንብረት ውድመት፣ ከዜጎች ሞትና መፈናቀል ባሻገር አብሮነትንና አንድነትን የሚሸረሽር ፈተናዎች ገጥመዋት ነበር።

ይህ ግጭት አያሌ ጥፋቶችን ቢያደርስም በቶሎ መፍትሄ ለማበጀት ውሳኔ ላይ መድረሳችን ከዚህም የከፋ አደጋ ውስጥ እንዳንወድቅ ታድጎናል። ይሁን እንጂ ውሳኔያችን ለጊዜው ለማህበረሰቡ እረፍት የሰጠና ከባድ ግጭቶችን የገታ ቢሆንም፣ በዘላቂነት በውይይት መፈታት ያለባቸው አሁንም ድረስ መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች እንዳሉብን መዘንጋት የለብንም። እነዚህን ችግሮች በሰከነና በሠለጠነ መንገድ ለመፍታት ዝግጁ ልንሆን ይገባል። ለዚህ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ አያሌ እድሎች ፈጥረዋል።

ለዘመናት የቆዩ ቁርሾዎችን ፈር ለማስያዝ፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት እና በንግግር ብቻ ለመፍታት፣ የልማት፣ የወሰን ግጭት እና ሌሎችም አያሌ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ለማስቻል በቅርቡ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን መቋቋሙ አይዘነጋም። ይህ ኮሚሽን "በፍፁም ተቀራርበን ማውራት አንችልም" በሚል ቁርሾ ፈጥረው ፅንፍ የያዙ ፖለቲከኞችን ወደ አንድ ጠረጴዛ ለማምጣት ሃላፊነት ወስዶ እየሰራ ይገኛል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን የሚመሩት አካላት በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በተፈጠሩ ልዩነቶች በውይይት ዘላቂ ዕልባት መስጠት የሚያስችሉ ህዝባዊ ምክክሮችን በማካሄድ ችግሮችን ለይቶ በጥናት የተደገፈ መፍትሄ ለማመላከት እንደሚሰራ በተለያየ ጊዜ ሲናገሩ አዳምጠናል።

ለዚህም አካታችና አሳታፊ፣ ገለልተኛ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ትብብር፣ ሕጋዊነትና ተዓማኒነትን መሰረት ያደረገ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸውን ነግረውናል። በምክክር መድረኩ በተከታታይ የሚሳተፉ አካላትን የመምረጥ ስራም እያከናወኑ መሆኑን በተለያየ መገናኛ ብዙሃን አድርሰውናል።

በርግጥ በጦርነት እና ቃታ በመሳሳብ ለችግሮቻችን መፍትሄ እንደማናገኝ በተጨባጭ ተምረናል። በተቃራኒው ጥቂት የመወያያ አብሮ የመስራት በር በመከፈቱ ምክንያት "እንደ አይጥና ድመት" የሚተያዩ ሰዎች ጭምር አብረው ሲሰሩና ውጤት ሲያመጡ ተመልክተናል።

በመሆኑን ዛሬም ድረስ ለቆዩት ችግሮቻችን መፍትሄው ውይይት፣ መፍትሄው ልዩነትን አቻችሎ አብሮ ለመስራት ቁርጠኝነት ማሳየት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ከዚህ መነሻ አገራዊ ውይይቱን እና አመቻች አካላትን በፍፁም ፍቃደኝነትና ቅን ልቦና ልንደግፋቸውና በጋራ አብረን ልንሰራ ይገባል።

ምሁራን፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ጦር የሰበቁ አካላት ሁሉም በየፊናቸው የሚያነሱት የልዩነት ጥያቄዎች ሊኖራቸው ይችላል። የማያግባቡ "ሊያቀራርቡ አይችሉም" ተብለው የሚታሰቡ ጫፍና ጫፍ የረገጡ ርእሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችም አይጠፉም። በዚህ ምክንያት ማንኛውም ፖለቲከኛ ምሁርም ይሁን የማህበረሰብ ክፍል ልዩነቶቹን ወደ ጠረጴዛው ይዞ ከመምጣት ሊያፈገፍግና የተለየ አማራጭ ሊፈልግ አይገባም።

ማእቀፍ ሉዓላዊነትን በማይጥስ አግባብ ሃሳቦቹን ይዞ ሊመካከርና በጋራ መፍትሄ ሊፈልግ እንደሚገባ መታመን አለበት። አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑም ለእቅዱ መሳካትም ሆነ ለኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ሲባል ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ለማካተትና ውክልና እንዲያገኙ ለማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ ተገቢውን እውቅና ሊሰጠውም ይገባል።

"አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንደሚባለው አገራዊ ብሂል መጪውን ትውልድ ዳግም በማይፈትኑ፣ የአገር ህልውናን እና ሉዓላዊነትን በሚያስጠብቁ መልኩ በጥልቅ ውይይትና መፍትሄ አመላካች ሳይንሳዊ መንገዶች ችግሮቻችንን መፍታት ይኖርብናል። ለዚህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልዩነት ባላቸው አካላት መካከል እየተመለከትን የምንገኘው የሚበረታታ መቀራረብ፣ አብሮ ለመስራት የሚያስችል ግንኙነት ሊበረታታና ሊቀጥል ይገባል።

አገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ከምንከተለው ሳይንሳዊ መንገድ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊ እሴቶችን የሚያጎሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይኖርብናል። ለአገር በቀል እውቀቶች ባህላዊ ሀብቶች እንዲሁም የልዩነትና ግጭት አፈታት ሥርዓቶችም ቦታ መስጠት አለብን። ይህንን በቅን ልቦና በፍፁም ቁርጠኝነት መተግበር ከቻልን ግጭትና ጦርነትን አቁመን ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ለመምጣት ፍቃደኛ እንደሆንነውና እራሳችንን በመልካም መንገድ እንዳሸነፍነው ሁሉ ዳግም በተመሳሳይ መልኩ በውይይት ከችግሮቻችን በላይ መሆናችንን በተጨባጭ ማስመስከር ይጠብቅብናል።

በተጨማሪም ለአገራዊ ችግሮቻችን በውይይት ለመፍታት የጀመርነው አዲስ መንገድ አስቀድሞ ህዝቡ ምን ይፈልጋል? የሚለውን ተረድቶ ባህልና ወጉን መሠረት ባደረገ መንገድ ምላሽ መፈለግን ያካተተ ሊሆን ይገባል ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ለመነጋገር መቀራረባችን በራሱ ድል መሆኑን ተገንዝበን ለመጪው ትውልድ ከግጭት ነጻ የሆነች ሰላማዊ አገር ለመፍጠር የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን ጥረት በሁለንተናዊ መልኩ መደገፍ ይጠበቅብናል። ሰላም!

ማእቀፍ ሉዓላዊነትን በማይጥስ አግባብ ሃሳቦቹን ይዞ ሊመካከርና በጋራ መፍትሄ ሊፈልግ እንደሚገባ መታመን አለበት:: አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑም ለእቅዱ መሳካትም ሆነ ለኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ሲባል ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ለማካተትና ውክልና እንዲያገኙ ለማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ ተገቢውን እውቅና ሊሰጠውም ይገባል

# በሲዳማ ክልል አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በሌማት ትሩፋት ተሳታፊ ሆነዋል

## - የወተት ምርትን በማቀነባበር ለጎረቤት ሀገራት እየተላከ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ከ997 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችና ወጣቶች እየተሳተፉ መሆናቸውን የክልሉ የእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ:: የወተት ምርትን በማቀነባበር ለጎረቤት ሃገራት እየተላከ እንደሚገኝም አስታውቋል::

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ተክሌ ጃምቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ከ997 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችና ወጣቶች ተሳታፊ ሆነዋል::

በክልሉ በዶሮ፣ በማር፣ አሳ፣ ወተት እና ሃር ልማት በክላስተር የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ተጀምሮ እንደነበር የተናገሩት ኃላፊው፤ በክልሉ ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶሮዎች ለአርሶ አደሮች ተሰራጭተው 309 ሺህ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል::

አንድ ሺህ 700 ከኮሌጅ እና ከዩኒቨርሲቲ የወጡ ወጣቶች ከተፈለፈሉ አንድ ቀን የሆናቸውን ጫጩቶች በመውሰድ እና በማራባት ሥራ ላይ ተሰማርተው እየሰሩ እንደሚገኙ እና ይህም ቋሚ የስራ ዕድል እንደፈጠረላቸው አክለው ገልጸዋል::


**አቶ ተክሌ ጀምቦ**

የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻልና የወተት ዘርፉን ለማነቃቃት እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ተክሌ፤ 93 ሺህ እንስሳት ዝርያቸው መሻሻሉንና በዘርፉ በተለያየ መልኩ ለአራት ሺህ 700 ወጣቶች የስራ ዕድል መፈጠሩን ተናግረዋል:: በወተት ዘርፍም 378 ሺህ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን አብራርተዋል::

በሃር ልማት ዘርፍ በ10 ወረዳዎች 310 ወጣቶች ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን አስረድተው፤ በአሳ ምርት ዘርፍም በአባያ እና በሃዋሳ ሐይቆች ላይ ወጣቶች በማኅበር ተደራጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል:: በአባያ ሐይቅ 150 ወጣቶች፤ በሀዋሳ ሐይቅ ደግሞ 210 ወጣቶች እየሰሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ በጓሮ አሳ ልማትም 280 አባወራዎች ተጠቃሚ ናቸው ብለዋል::

እንደ አቶ ተክሌ ማብራሪያ፤ በክልሉ የወተት ምርትን በማቀነባበር ለኤርትራ፣ ጁቡቲ እና ሱዳን እየተላከ ይገኛል:: በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ለከብቶቹ የተሻለ መኖን በማቅረብ፣ የተሻሉ ዝርያዎችን ከውጭ ሃገራት በማስገባት እና የአስተዳደር ስራዎችን በማሻሻል 327 ሺህ ቶን ወተት ለማግኘት ታቅዶ አሁን ላይ 303 ሺህ ቶን የወተት ምርት እየተገኘ ነው::

# የመጪው ትውልድ እምቅ አቅም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቢሮ ለስምንተኛ ጊዜ ያዘጋጀው የሳይንስ ፈጠራ አውደ ርዕይ ቢሮው በከተማዋ ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች በሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ላይ ትኩረት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ አንዱ ማሳያ ነው:: በአውደ ርዕዩም በርካታ ተማሪዎችና መምህሮቻቸው የተሳተፉ ሲሆን አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችንም ይዘው የቀረቡበት ነው::

በአውደ ርዕዩ ላይ የኮልፌ ቀራኒዮ ሬይኔሰንስ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪ በረከት ጌቱ በባትሪ የሚሰራ ርሆቦት ይዞ ቀርቧል:: የሰራው ርሆቦት በተለይም ለኦቲዝም ታማሚዎች ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ ችግር ፈቺ የፈጠራ ስራ መሆኑን ተናግሯል::

ተማሪ በረከት የሰራው ርሆቦት አንዴ ባትሪው ቻርጅ ከተደረገ ሙሉ ቀን አገልግሎት መስጠት የሚችልና የአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞና እንግሊዘኛ ቋንቋን የመረዳት ችሎታ ያለው ነው ይላል:: ርሆቦቱ የሰውን ባህሪ እና ስሜት በማየት እና አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ለተቆጣጣሪው አካል በማሳወቅ ለኦቲዝም ታማሚዎች እንደሞግዚትነት የሚያገለግል ነው ሲል የፈጠራ ስራውን አስረድቷል::

በሚኖርበት አካባቢ ያሉ የኦቲዝም ታማሚዎች ችግር ለፈጠራ ስራው እንዳነሳሳው የገለጸው ተማሪው፤ ፈጠራውም ወደፊት ለታማሚዎችና ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ትልቅ ሚና ይኖረዋል:: አውደ ርዕዩም የተማረውን በተግባር ለመስራት እንዳስቻለው፣ የፈጠራ ስራውን ለህብረተሰቡ እንዲያስተዋውቅና ከሌሎች ጋር ልምድ ለመለዋወጥ እድል እንደፈጠረለት ተናግሯል::

ለወደፊቱም ከዚህ የበለጠ የፈጠራ ስራ ለመስራት የቁሳቁስ ድጋፍና ሙያዊ ክትትል እንዲደረግላቸው ገልጾ፤ እንደዚህ ዓይነት መርሀ-ግብር ቀጣይነት ቢኖራቸው ብዙ ሥራ ፈጣሪዎችን ማፍራት ይቻላል ሲል ተናግሯል::

ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች የሚያገለግል በባትሪ የሚሰራ የገላ እና ጸጉር መታጠቢያ የፈጠራ ስራ ይዛ የመጣችውና በእትጌ መነን አዳሪ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ተማሪ እየሩሳሌም ታደሰ በበኩሏ፤ እንደዚህ አይነት ምቹ ሁኔታና ግብዓት ሲመቻች ብዙ አቅምና ችሎታ ያላቸው የፈጠራ ባለሙያዎች እንዲበረታቱና ለችግሮች መፍትሄ ለመስጠት እንደሚያስችል ተናግራለች::

ሌላው የፈጠራ ውጤት ባለቤት ተማሪ ሰያ አማኑኤል ከአካባቢው በተገኙ ቁሳቁሶች በመጠቀም አንዴ ቻርጅ ከተደረገ ለሶስት ቀናት የሚቆይና ባሉበት ሆነው ለጽዳት አገልግሎት የሚውል የቆሻሻ ማንሻ የሰራ ሲሆን፤ ፈጠራው ገጠራማ አካባቢ ለሚገኙ ነዋሪዎች ብሎም የጽዳት ሰራተኞች ስራቸውን ቀላልና ምቹ የሚያደርግ ነው::

ተማሪ ሰያ ለወደፊት የተሻለ ትውልድ ለመፍጠር ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሊሳተፍበት የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት የአዉደ ርዕዩን ተደራሽነትን ማስፋትና ማጠናከር ይኖርበታል ብሏል::

በአውደ ርዕዩ ላይ እየጎበኘ ያገኘነው ተማሪ ኡርቃ ታምሩ በጉብኝቱ እንደተደሰተ ተናግሮ፤ ከዚህ በፊት አይቶትና ሰምቶት የማያውቃቸውን የፈጠራ ሥራዎች መጎብኘቱን ገልጿል:: ሀገራችን በፈጠራ ሥራ በኩል ዕድገት ላይ በመሆኗ ለቀጣይም እርሱም በዚህ የፈጠራ ሥራ ላይ ተሳታፊ ለመሆን እንዳነሳሳው ተናግሯል::

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በፍጥነት እያደጉ ከሚገኙት ሀገራት ውስጥ የምትጠቀስ ሲሆን፤ የቀጣዩ ትውልድ ላይ እየተሰራ ያለው ስራ ችግር ፈቺ ግኝቶችን ለማፍለቅ ያስችላል:: ሀገርንም ያሳድጋል፤ እናም መንግስት የፈጠራ ሥራዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በትኩረት መስራት አለበት ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል::

# ዩኒቨርሲቲው በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግቦች ላይ የተጠቀሱትን 16 ነጥቦች ያማከለ ስለመሆኑ ቅድመ ግምገማ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የዘላቂ ልማት ግቦች ላይ ያተኮሩ ምርምሮች በብዛት ለፖሊሲ ግብዓትነት ያገለግላሉ ያሉት ፕሮፌሰሯ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተቋማት ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶች በማከናወን እያቀረበ መሆኑን ጠቁመዋል።

በዩኒቨርሲቲው የሃገር ልማት ጥናት ኮሌጅ ዲን ዶክተር ተስፋዬ ዘለቀ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ የተጀመረውን የዘላቂ ልማት ግቦች ለማሳካት ኮሌጁ ባለፉት ዓመታት ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጥናትና ምርምሮችን ሲያካሂድ መቆየቱን ገልጸዋል።

በኮሌጁ የሚገኙ 11 የትምህርት ክፍሎች ከዘላቂ የልማት ግቦች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች እያከናወኑ ይገኛል ያሉት ዶክተር ተስፋዬ፤ የአደጋ ስጋትና አመራር፣ የገጠርና የአካባቢ ልማት፣ በስነ ህዝብ፣ በስርዓተ ጾታና በሌሎችም ዘርፎች የምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በጋራ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

በጨርቃጨርቅ፣ በአበባ ልማትና በሌሎች የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ ሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የሚያጎለብትና ከአምስት በላይ ከተሞችን ያካተቱ ጥናቶች በሂደት ላይ ይገኛል ያሉት ዶክተር ተስፋዬ፤ ጥናቶቹ ሲጠናቀቁ የሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል ሲሉ ተናግረዋል።

ምርምሮችን ተግባራዊ በማድረግና የልማት እንቅስቃሴዎችን ከመደገፍ አኳያ የዓባይ ተፋሰስ የሚነሳበትን የጮቄ ስነ-ምህዳር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የነበሩ የኮሌጁ ፕሮጀክቶችና ተመራማሪዎች እንደነበሩ በመግለጽ፤ በተጨማሪም በወረዳዎችና ዞኖች የአርሶ አደሩን ህይወት የሚቀይሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል፡፡

አየር ንብረት ለውጥን ጨምሮ ሀገራዊ ዕድገትን የሚያፋጥኑ ምክረ ሀሳቦችን በምርምር በማስደገፍ እየቀረቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር በዘላቂ ልማት ግቦች አተገባበር፣ ፈተናዎችና ዕድሎች ላይ ያተኮረ የሦስት ቀናት ጉባኤ በቅርቡ ማከናወኑን ጠቁመው፤ ጉባኤው በርካታ የጥናትና ምርምር ጽሁፎች የቀረቡበት መሆኑን በመግለጽ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ውጤቶች ተገኝቶባቸዋል ብለዋል።

በቀጣይም የልማት ስራዎች ከዘላቂ የልማት ግቦች ጋር በተናበበ መልኩ ለማከናወን የሚረዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

# በሽግግር ፍትህ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ክልሎች እንደሚካሄድና መስከረም ወር ላይ ያለቀለት የፖሊሲ ሰነድ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ተገልጿል::

በፍትህ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አወል ሱልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ለማውጣት የሚያስችል ጥናት በባለሙያዎች ቡድን ሲጠና ቆይቷል:: ጥናቱ ተጠናቅቆ የፖሊሲ አማራጭ ጽሁፎች ሰነድ ተዘጋጅቶ በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ምሁራንና የህብረተሰብ ክፍሎች ተወያይተውበታል:: በሁሉም ክልሎች የሚደረገው ግብዓት የማሰበሰብ ውይይቱ ሐምሌ ወር ላይ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም ያለቀለት የፖሊሲ ሰነድ ለሕዝብ ይቀርባል::

ፖሊሲውን ከመጀመሪያው ሕዝቡ የመከረበት እንደሆነ የጠቆሙት አቶ አወል፤ በአሁኑ ወቅትም በአማራጭ የፖሊሲ ሰነድ ላይ የግብዓት የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል:: እስካሁን በተካሄዱት የግብዓት ማሰባሰብ ውይይቶች የተሳኩ እንደነበርና፤ የቀረቡ የሀሳብ አማራጮች ላይ አብዛኛው ማኅበረሰብ መደገፉንም ጠቅሰዋል::

አቶ አወል፤ የፖሊሲ አማራጭ የያዘው ሰነድ ከቀረበ በኋላ ሰነዶቹ ላይ ከወራት በፊት ውይይት መጀመሩን ገልጸዋል:: በመላው ሀገሪቱ በርካታ መድረኮች ይካሄዳሉ ተብሎ ዕቅድ ተይዞ በዚሁ መሠረት ዕቅድ ተዘጋጅቶለት ውይይቶች ሲደረጉ እንደቆዩ ጠቅሰዋል:: እስካሁን በኦሮሚያ ክልል ብቻ በ53 ከተሞች ላይ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ማወያየት እንደተቻለ አውስተዋል::

በአሁኑ ወቅት ውይይቱ በደቡብ ክልል ባሉ ከተሞች እየተካሄደ እንዳለም ጠቁመዋል:: በአሮሚያና በደቡብ ክልል የተደረጉት ውይይቶች በሁሉም ክልሎች እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል::

እያንዳንዱ መድረክ ላይ አማራጭ ፖሊሲዎች በባለሙያዎች እየቀረቡ ሕዝቡ እንዲገነዘበውና ሃሳቡን በነጻነት እንዲገልጽ የቡድን ውይይት ጭምር እየተደረገ ግብዓት እየተሰበሰ መሆኑን አስታውቀዋል:: በውይይቶች የተገኙት ግብዓቶች ሰነዱን ፖሊሲ አድርጎ ለማውጣት ጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል::

እንደ አቶ አወል ገለጻ፤ ውይይቶቹ እስከ ሀምሌ መጨረሻ ያበቃሉ ተብሎ የታቀደ ሲሆን፣ ከሀምሌ እስከ መስከረም የተሰበሰቡትን ግብዓቶች ሰነዱ ላይ ታክሎ የተመረጡ ሀሳቦችን በፖሊሲ አካትቶ የመሄድ ዕቅድ ተቀምጧል:: መስከረም ወር 2016 ዓ.ም ላይ ያለቀለት የፖሊሲ ሰነድ ለሕዝብ የሚቀርብ ይሆናል::

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ መደበኛ በሆነው የፍትህ አስተዳደር ውስጥ ሊፈቱ የማይችሉ ሰፋፊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ጨምሮ በማኅበረሰቡ መካከል የተከሰቱ ሰፋፊ ቁስሎችን ለመሻርና ለማዳን አዎንታዊ ሚና እንዳለው አቶ አወል አስገንዝበዋል::

በመደበኛው የወንጀል ፍትህ ስርዓት ሰብዓዊ ጥሰት ላይ ሚና የነበራቸው ሰዎች በወንጀል እንዲጠየቁ ከማድረግ ውጪ ሌላ ነገር ማድረግ አይቻልም ያሉት አቶ አወል፤ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ውስጥ ግን ርምጃዎች ሲወሰዱ በአማራጮች እንደሆነ ተናግረዋል:: እነዚህም የወንጀል ተጠያቂነትን ማስፈን፣ የእርቅ ሥርዓት መፈጸም፣ እውነትን ማፈላለግ፣ ማካካሻና የመሳሰሉ ናቸው ብለዋል::

የሽግግር ፍትህ፤ የተለያዩ አማራጮችን ወስዶ ማኅበረሰቡ ላይ የተፈጠረውን ቅሬታ ቁስሉን ሽሮ በቀጣይ ማህበረሰቡ እርስ በእርሱ እንዲዋደድ፣ እንዲቻቻል፣ እንዲከባበርና የቀደመ እሴቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ያስችላልም ሲሉ ገልጸዋል::

# አዲሱ”ዓባይ ፪” መርከብ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

፪” መርከብ ቀደም ሲል በነዳጅ ጫኝ መርከቦች ሲደርስ የነበረውን ኪሳራ ማስቀረት ያስችላል፡፡

አዲሱ መርከብ በቀን 11 ሺህ ዶላር የተጣራ ትርፍ ገቢ ለድርጅቱ የሚያስገኝ በመሆኑ በ60 ቀናትም 660 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ገቢ እንደሚያስገኝ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ደምሰው ገለጻ፤ ባህር ዳርና ሀዋሳ የተሰኙት ሁለት ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ከ11 ዓመታት በፊት የሀገሪቱን ነዳጅ እንዲጭኑ ታሳቢ ተደርጎ የተገዙ ነበሩ። እነዚህም መርከቦች በድርጅቱ ታሪክ የመጀመሪያ በሆነው 63 ሺህ 500 ቶን የመጫን አቅም ባለው ግዙፉ መርከብ በድርድር ተቀይሯል።

“ዓባይ ፪” የተሰኘ ግዙፍ መርከብ ድርጅቱን ለመርከቦች ኪራይ ሲያወጣው የነበረውን ወጪ ያስቀራል ያሉት አቶ ደምሰው፤ የአፈር ማዳበሪያ ጭነቶችን ለማከናወን የሚረዳ ነው፡፡ መርከቡ ወደ ስራ በመግባት የድርጅቱን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ሁለቱን የቀድሞ መርከቦች በ”ዓባይ ፪” ለመቀየር ካስገደዱ ጉዳዮች መካከል የውጭ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅቶች በሁለቱ ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ለመጠቀም እምቢተኝነት ማሳየታቸው አንዱ መሆኑን አውስተው፤ መርከቦቹን ለሌሎች ድርጅቶች በኪራይ እንዲሰሩ ለማድረግ የተሞከረ ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አለመቻሉን ተናግረዋል፡፡

ሁለቱ መርከቦች የራሳቸውን ወጪ ለመሸፈን በማያስችል መልኩ ስራ አልባ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የነዳጅ ጫኝ መርከቦቹ የመጫን አቅም 42 ሺህ ቶን መሆኑን የገለጹት አቶ ደምሰው፤ ይህም መካከለኛ የመጫን አቅም ካላቸው መርከቦች ውስጥ የሚያስመድባቸው በመሆኑ 50ሺ ቶን የመጫን አቅም ካላቸው መርከቦች በዝቅተኛው ደረጃ ያስቀመጠና ተፈላጊነታቸው በመቀነሱ ለኩባንያዎች አከራይቶ ለመጠቀም ፈተና መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከድርጅቱ ለመርከብ ማንቀሳቀሻ ጨምሮ ለነዳጅና ለመርከበኞች ከፍተኛ ወጪ ይወጣ እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህም ለኪሳራ እየዳረገው መምጣቱ በጥናት ተረጋግጧል ብለዋል፡፡

የቀድሞዎቹ ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ሽኝትና የግዙፉ አልትራማክስ መርከብ ቅበላ የተካሄደ መሆኑን በመግለጽ፤ ይህም ድርጅቱን በበላይነት በሚመሩ አካላት ዕውቅና የተካሄደ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአልትራማክሱ መርከብ ፈርጀ ብዙ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ዓባይ ፪ መርከብ ለድርጅቱ ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ክብርና ኩራት መሆኑን አመላክተዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ፍቅር እስከ መቃብር እና ሰው መሆን ምንና ምን ናቸው ?

(የመጀመሪያ ክፍል)

ሽሽት ላይ ነኝ ። በሴራፖለቲካ ፣ በበሬ ወለደና በግነት ያበደ ሟርት ፣ መርዶንና መባተትን የማምለጥ ሽሽት ። የገባንበትና እያለፍነው ያለው ወጀብ ፣ ማዕበልና ቀውስ ሳያንስ ፤ ቀውስን ፣ ሞትን፣ ግዳይን፣ መፈናቀልን ፣ ኀዘንንና መከራን እንደ ምርጥ ዘር ከሚያባዛው ዩቲውበር ፣ ፌስቡከኛ ፣ ቴሌግራመኛ ቲዊተረኛ ፣ ቲክቶከኛ ፣ ቴሌቪዥንኛና "ጋዜጠኛ" ሽሽት ላይ ነኝ። አዎ ! ከመርዶ ፣ ከለቅሶ፣ ከዋይታ ፣ ከጭንቀት፣ ከድብርት ፣ ከመብሰክሰክና ከመብሰልሰል ውጭ መፍትሔና ጥሩ ዜና ጠብ ከማይለው ማህበራዊ ሚዲያ ኃይለኛ ሽሽት ላይ ነኝ። ሽሽቱ አንዳንድ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ያካትታል።

ከቴሌቪዥን ቻናል ስሸሽ ፣ ስዘልና ስቅበዘበዝ ነው ከ"ebs ውሎ" ጋር ፊት ለፊት የተገጣጠምሁት። ጋዜጠኛዋ ውሎ የምታደርገው እናቱ "ሰው መሆኔ "አይቀርም ብላ የህልሟን ዘር በዘራችበትና ሰውመሆን ስትል ስም ባወጣችለት "ሰውመሆን" ይስማው ጋር ነው ። አዎ ወላጅ እናቱ ልጇ ለወግ ለማዕረግ በቅቶ፤ እሷም አምስት የልጅ ልጅ አይታ በሰውመሆን ሰው ሆናለች ። ስምን መልዓክ ያወጣል አይደል ብሂሉስ። "አንድ ቀን ሰው እሆናለሁ።" ማለት ሌላ አይደለም ህልሜ እውን ሆኖ አያለሁ ነው ። ችግሩ ፣ መከራውና ፈተናው አልፎልኝ አያለሁ ። ያሰብሁት ሰምሮልኝና ተሳክቶልኝ ሰው ከደረሰበት እደርሳለሁ ። እሱም እንደ ስሙም እንደናቱም ሰውሆኗል ። አንድ ቀን ሰውመሆኔ አይቀርም ብሎ እንዳለመውና ርዕይ እንዳደረገው ፤ ሰውመሆን ይስማው ሰው ሆኗል ። የልጅነት ሕልሙን በመኖር ሰውመሆን ሰው ሁኗል ። በልጅነቱ የተቆራኘውን የፊልም ፍቅር ፤ አንድ ጊዜ ደራሲ ፣ ሌላ ጊዜ ፕሮዲውሰር ወዲህ ዳይሬክተር ወዲያ ሲኒማቶግራፈር በመሆን እንደ ዝሀ ዘጊ እየተመላለሰበት ሰውመሆን ሰው ሆኗል ። በ16 ፊልሞችና ከዚህ በማይተናነሱ የሙዚቃ ክሊፖች ተንሸራሽሯል።

ሰው መሆንን የስኬት ፣ የስምረትና የውጤት መገለጫ ሲደረግ የተዋጣለትና የተሳካለት ነገር ሊገለጽበት ይችላል ። አምባሳደር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን የገለማውንና የጨረተውን የፊውዳል ሥርዓት በተዋበ ቋንቋ ፣ በማይረሱና ህያው በሆኑ ገጸ ባህሪያት ፣ በተዋጣለት ትልም ፣ ሴራ አወቃቀር ፣ ግጭት ፣ ጡዘት ፣ ልቀትና አተራረክ የህያው ስትንፋስ በአፍንጫው እፍ ብለው ሕይወት ዘሩበት ። በሰውመሆንኛ አነጋገር ያን የበሰበሰን ሥርዓት ሰው አደረጉት ። ዘመንና ትውልድን አሻገሩት ። ዘመንና ትውልድ ያረጃል። ያልፋል እንጂ "ፍቅር እስከ መቃብር" ዛሬም ብላቴና ፤ ዛሬም ወጣት፤ ዛሬም ህያው ነው ። ገና የሚመጣውና የሚሄደው ትውልድ ይቀባበለዋል ። በፊጌታው ወጋየሁ ንጋቱ ደግሞ በወርቃማ ድምጹ ፤ ትንግርተኛ ፣ ምትሀተኛ፣ ተአምረኛና አስማተኛ በሆነ አተራረኩ "ፍቅር እስከ መቃብር"ዳግም ወለደው። ሰው አደረገው ። አድማስ ገመገሙን አሻግሮ በየህይወታችን በየቀያችን ኖኘው ። አደረሰው ።

አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ወይም ቴዲ አፍሮ ደግሞ በ"ማር እስከ ጧፍ"ወይም "ፍቅር እስከ መቃብር"በሚል ትውልድና ዘመን ተሻጋሪ ሙዚቃውና በተዋጣለት የዘፈን ግጥም ፣ ጆሮ ገብ በሆነው ቅንብሩና ዜማው በጣት በሚቆጠሩ ደቂቃዎች ፤ 552 ገጽ ያለውን ረጅም ልብ ወለድ በሙዚቃ እንደገና አስነበበን። ከአእምሮ ጓዳችን ቀስቀሶ በእዝነ ህሊናችን ህያው አደረገው ። ሰውአደረገው ። አቧራውን አራግፈን እንደ አዲስ በጉጉት እንድናነበው አደረገን ። የሙዚቃ ክሊፑን ተከትሎ አዲሱ ትውልድም የፍቅር እስከ መቃብር ያለህ አለ ። በተደጋጋሚ ታተመ ። እንደ ከረሚላ ተቸበቸበ ።

ዘመንን ሽሮ ፣ ርቀትን አጥፍቶ ተራርቀው የነበሩ ትውልዶችን ድልድይ ሆኖ አገለገለ ። ለተጨማሪ ህትመቶች ምክንያት ሆነ ። ከዚህ ድንገቴ ፈንጠዝያ አንጎቨር በቅጡ ሳንወጣ ፤ "ማር እስከ ጧፍ" ወይም "ፍቅር እስከ መቃብር" በክሊፕ መጣና ሁላችንንም ያለ ልዩነት ጉድ አስባለን ። 10 ደቂቃ ባልሞላ የሙዚቃ ክሊፕ "ፍቅር እስከ መቃብር" ግዘፍ ነስቶና ስጋ ለብሶ ተገለጠ ። ወጋየሁ ንጋቱ አንድ ጊዜ ሕይወት ዘራበት ። ቴዲ አፍሮ ግን በዘፈን ግጥሙ በየአእምሮ ጓዳችን አመላለሰው ፣ በሙዚቃና በዜማ አስውቦ አይረሴ አደረገው ። በክሊፑ ከምናባዊነት አውጥቶ በእያንዳንዳችን አእምሮ ሐውልት አቆመለት። ደጋግመው ቢያነቡት የማይጠገበውን ረጅም ልቦለድ፤ ደጋግመው ቢመለከቱት የማይጠገብ ክሊፕ አደረገው። ፍቅር እስከ መቃብርን ከአንድም ሁለት ሶስት ጊዜ ፈጠረው ። ሰው አደረገው ።

ለምን ግን እንደሌሎች ታላላቅ ድርሰቶች ወይም ማስተርፒሶች ወደ ፊልም አልተቀየረም የሚለውን የትውልዶች ጥያቄና ቁጭት እንደ አዲስ አጫረው። በክሊፑ እንደሚቻል አስረግጦልን አደፋፈረን ። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቴዲ አፍሮ ካጀገናቸውና ካደፋፈራቸው ተቋማት አንዱ ነው ማለት ይቻላል ። በድፍረትና በልበ ሙሉነት "ፍቅር እስከ መቃብር"ን በተከታታይ ፊልምነት ለመስራት ወኔ እንዲሰንቅ አድርጎታል ። እውነት ለመናገር የኢቲቪ የወቅቱን አመራር ለዚህ ቆራጥና ደፋር ውሳኔው አለማድነቅ ንፉግነት ነው ። ከመቀመጫዬ ተነስቼ ባርኔጣዬን ከፍ አድርጌያለሁ ። ETV/EBC "ፍቅር እስከ መቃብር"ን ሙሉሰው ሊያደርገው ውል ያሰረው ፤ ከዘመን አይሽሬና አይረሴ "ማር እስከ ጧፍ"ወይም "ፍቅር እስከ መቃብር"ክሊፕ ጀርባ የማይተካ ሚና ከተጫወቱ እንቁ ባለሙያዎች አንዱ በሆነውና በሲኒማቶግራፈርነት ከተሳተፈው ዳይሬክተርና ሲኒማቶግራፈር ሰውመሆን ይስማው ጋር መሆኑ "ፍቅር እስከ መቃብር" በአስተማማኝ ሰው እጅ ላይ እንዳረፈ እንዲሰማኝ አድርጓል ።

ለምን ብትሉ በአምስት ወር ውስጥ በዩቲውብ ወደ 8,000,000/ስምንት ሚሊዮን/የሚጠጋ እይታ ያገኘው የአስቻለው ፈጠነ/አርዲ/ "እናትዋ ጎንደር" እንዲሁም ከአንድ ወር በፊት በዩቲውብ ተለቆ ወደ 2,000,000/ሁለት ሚሊዮን/እይታ ያገኘው የዚሁ ሀገረሰብኛና ቱባ አቀንቃኝ አርዲ ስራ የሆነውን "ካሲናው ጎጃም"ን በሲኒማቶግራፈርነትና በዳይሬክተርነት ያዘጋጀው ሰውመሆን ስለሆነ "ፍቅር እስከ መቃብር" ምንም ከክሊፕ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች የራቀ ፤ ትውልድና ዘመን ተሻጋሪ ማስተፒስ እና የአገር ቅርስ ስለሆነ የፊልም ስራው ሕዝብ በጉጉት ብዙ የሚጠብቅበት ስለሆነ ኃላፊነቱ ከባድ ነው ። በነገራችን ላይ እነዚህ ክሊፖች ጎጃምና ጎንደር ማዶ ለማዶ ነው የሚለውን የአበው ይትበህል የሻረ ሆኖ ይሰማኛል ። በ"እናትዋ ጎንደር" እና በ"በካሲናው ጎጃም" ጎጃምና ጎንደር ማዶ ለማዶ መሆናቸው ቀርቶ ቤተኛ ሆነው ተመልክተናል ።

ወደ "ፍቅር እስከ መቃብር"ፊልም የመሆን ነገር ስንመለስ ፤ ሰውመሆንና ለዚሁ ሥራ የሚያዋቅረው ቡድን ይህን ወርቃማ እድል ላለማባከንና ለማሳካት ብርቱ ጥንቃቄ ይጠበቅበታል ። እንደ ኖሊውድ ፣ ቦሊውድና ሆሊውድ ባሉ ኩባንያዎች እንደ "ፍቅር እስከ መቃብር" ያሉ ክላሲካል ልቦለዶች እንዴት ፊልምነት እንደተቀየሩ ልምድ መቀመር ፤ ዓለምአቀፍ ባለሙያዎችን ማሰተፍ ይጠበቅበታል፡ ታላቁን የፊልም ሰው ኃይሌ ገሪማን ልብ ይሏል ። የሰው ሰራሽ አስተውሎትንም ወይም AI በብቃት መጠቀም ስለመቻሉ እርግጠኛ መሆን አለበት ። ፊልሙን ከEBC አድማስ ባሻገር ዓለምአቀፋዊ ለማድረግ ፤ እንደነ ኖሊውድ የኢትዮውድ መሰረት የሚጣልበት ፤

የአገራችን የፊልም ኢንዱስትሪም ወሳኝ መታጠፊያ critical juncture ፤ የአገሪቱን ገጽታ ለመገንባትና የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃት ከሁሉም በላይ የማያዳግም ዘመን ፣ ትውልድ ፣ የቆዳ ቀለም ፣ ድንበር፣ ዘር ፣ ሃይማኖት ፣ ወዘተረፈ የተሻገረ ስራ ለመስራት አሁን ከተያዘለት ወጭ በላይ ከፍተኛ ወጭ ይጠይቃልና እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ኢትዮቴሌኮም ያሉ የአገር ምልክቶች ድጋፍ ያደርጋሉ ብዬ እጠብቃለሁ ። ለቀረጻና ለስርጭት መጣደፍ አያሻም ። ሰከን ማለት ያሻል ።

እንደ "ፍቅር እስከ መቃብር"ያለ ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ወይም ማስተርፒስ ሥራ ወደ ፊልም ሲቀየር ውስብስብ ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ ። ለፊልሙ እንዲመች የመጽሐፉን ታሪክ የመቀየር ፣ ታሪኩን ለፊልም እንዲመች ሲባል ማቅለል ወይም ሲምፕሊፋይ ማድረግ ፣ ድርጊት ወይም አክሽን ላይ የማተኮር አባዜ ፣ ገጸ ባህሪያትን መቀየር ፣ ለፊልሙ መነሻ የሆነውን ድርሰት ችላ የማለት ፣ ታሪኩን ማፍጠንና አጨራረሱን መቀየር ከተግዳሮቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከሁሉም በላይ ዘመን ተሻጋሪ የሆነውን "ፍቅር እስከ መቃብር"ወደ ፊልም ለመቀየር ሲታሰብ ድርሰቱን በጥልቅ መረዳት እና ለምን የተዋጣለት ዘመን ተሻጋሪና ተወዳጅ ሥራ እንደሆነ አላባውያንን ቁጭ ብሎ በጥሞና በቅጡ መገንዘብ ያሻል። ስራውን ዘመን ተሻጋሪ ላደረጉት ጭብጥ ፣ ገጸ ባህሪያትና ትልም መታመን ግድ ይላል ። ወደ ሲኒማቶግራፈርና ዳይሬክተር ሰውመሆን ይስማው ስመለስ በአንድ ወቅት የዶቸ ቬለዎች ተስፋለም ወልደየስና ሸዋዬ ለገሠ ወዳጠናከሩት ዘገባ እንመለስ።

የተዋጣለት ሲኒማቶግራፈርና ዳይሬክተር በአዳጊው የኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ አብዛኛውን ስራ የሚያከናውኑት ወጣቶች ናቸው ፡፡ በዘርፉ ካለው የሰው ኃይል እና የልምድ እጥረት የተነሳም በርካታ ዘርፎችን ደራርበው ሲሰሩ ይስተዋላል፡፡ ከእነዚህ ወጣቶች መካከል ጥቂቶቹ በሚሰሯቸው ፊልሞች እየተማሩ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ መሻሻል በማሳየት ላይ ይገኛሉ ፡፡ ሰውመሆን ይስማው አንዱ ነው ፡፡ ወጣቱ የፊልም ባለሙያ ሰውመሆን ይስማው በአስራ ስድስት የኢትዮጵያ ፊልሞች ላይ አሻራውን ያሳረፈ ነው ፡፡ የዘመን ተጋሪው ወጣቱ የፊልም ዳይሬክተር ዳዊት ተስፋዬ "ስለሰውመሆን ሲወራ" መረሳት የሌለበትን ይጠቁማል ፡፡ ሰውመሆን ሲኒማቶግራፈርም ፣ ዳይሬክተርም ፣ ስክሪን ፕሌይ ጸሀፊም ስለሆነ ስለሰውመሆን ስናወራ ስለየትኛው እንደሆነ ማወቅ ወሳኝ ነው ብዬ አስባለሁ ፡፡ የራሱ ቀለም ያለው፣ የሰራውን ሥራ አይተህ የሰውመሆን ሥራ ይመስላሉ የሚባሉ ሥራዎቹ ብዙ ናቸው ፡፡ በሰኒማቶግራፊም፣ በዳይሬክቲንግም ያ ነገር አለው ብዬ አስባለሁ" ይላል ዳዊት ፡፡

የሥነ መቼት እና የሜካፕ ባለሙያው ተስፋዬ ወንድማገኝ የሰውመሆን የቅርብ ጓደኛ ነው፡፡ የሰውመሆን የቅርብ ሰዎች እንደሚጠሩት ጓደኛውን "ሶሚክ" ነው የሚለው፡፡"እውነት ለመናገር ሰውመሆን 24 ሰዓት ስለፊልም የሚያወራ ፊልም የሚወድ ልጅ ብዙ ቮካብለሪ ያለው ልጅ ነው። ሶሚክ ከልጅነቱ ጀምሮ ያሳለፋቸው ጊዜያቶች በጠቅላላ ቀጥታ ወደፊልም ሥራ እያንደረደሩ ነው ያመጡት። ሁልጊዜ ስለአባቱ፣ እናቱ፣ ስለሰፈሩ ልጆች እንዳለ ታሪካቸውን በሚያወሪኝ ጊዜ በቃ ይሄ ልጅ ታሪክ ተናጋሪ እንዲሆን ተመርጧል ብዬ አስባለሁ። እርሱ ጋር ያለው የፊልም ፍቅር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመጣ ነገር ነው" ይላል ተስፋዬ፡፡

ጎንደር ተወልዶ ያደገው ሰውመሆን "የነፍስ ጥሪው" ወደተባለለት የፊልም ሙያ እንደው በቀጥታ ዘው አላለም፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲቀላቀልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ኮሌጅ ያጠናው "ፐርቼዚንግ" ነበር። ምንም እንኳ ትምህርቱ ንግድ ተኮር ቢሆንም ለዩኒቨርሲቲ ትምህርቱ በአዲስ አበባ መቆየቱ ወደ ፊልም ሥራ የሚሳብበትን አጋጣሚ ፈጥሮለታል፡፡

ሰውመሆን ትምህርቱን የሚከታተልበት የንግድ ሥራ ኮሌጅ የማደሪያ አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ አጎቱ ሻለቃ ተስፋዬ ይግረም ዘንድ እንዲያርፍ ይሆናል። ፎቶ አንሺ የሆኑትን አጎቱን ለመርዳት ከትምህርቱ ጎን እርሳቸው ፎቶ ቤት ያዘወትር ያዘ። ያኔ እንዳሆኑ ለአጠቃቀም ቀላል የሆኑ ዲጂታል ፎቶ ካሜራዎች አልነበሩም እና በአናሎግ ካሜራዎች ሲሰራ ቆየ፡፡ "አንዳንድ ሰርጎች አነሳ ነበር፡፡ ሌላም ሌላም ሥራዎች እየሰራሁ ከዚያ ቀስ ብሎ ከፎቶግራፍ ማንሳት ወደ ቪዲዮ መቅረጽ መጣ፡፡ ግን ምንድነው ከድሮም ጀምሮ ሲኒማ ላይ ለየት ያለ ፍላጎት ነበረኝ። ልጅ እያለሁ፣ ሁለተኛ ደረጃም ሆኜ ቪዲዮ ቤቶች አዘወትር ነበር፡፡ ሲኒማ ይሄ ታሪክ መንገር የሚባለው አካባቢ መንፈሴ ነበር፡፡ እና ቀስ እያለ ወደ ፊልም እያደገ መጣ" ይላል ያን ጊዜን ሲያስታውስ ፡፡

የቪዲዮ ፊልሞችን ለሰፈር ተመልካች የሚያከራይበት የራሱ ሱቅ የነበረው ሰውመሆን የመጀመሪያ ፊልሙን ሊሰራ ሲነሳ ከተለመደው ወጣ ያለ ነገር ለመሞከር ተነሳ፡፡ ከርዕሱ ጀምሮ ወጣ ያለ የነበረው ይህ ፊልም የወቅቱ መነጋገሪያ ነበር። "862" የተሰኘ ስያሜ ስለሰጠው ስለዚህ ፊልሙ ሰውመሆን ሲገልጽ "ቅዠት የመሰለ" ይለዋል፡፡ "ለምንድነው ፊልም ሀ፣ ለ፣ሐ...ተብሎ የሚተረከው?፡፡ ለምን ከመጨረሻ አይጀምርም? የሚል ፍልስፍና የነበረው ፊልም ነው ይገኜ የመጣሁት" ይላል ስለ መጀመሪያ ፊልሙ አካሄድ ሲናገር ፡፡ "ታሪኩ ወደ ፊት እየሄደ ወደ ኋላ ይመጣል። በጊዜው አንዳንድ ልጆች የፈረንጅ ተጽእኖ ያለበት ታሪክ ነገራ ዘዴ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

እኔ ደግሞ ከዚያ የተለየ ተቃራኒ የሆነ የእኛ ነው ብዬ ነበር የማምነው፡፡ ለምሳሌ ቢሊጮ የሚባል ገጸባህሪ ተረት ሲነግሩህ 'ቢሊጮ ከዚያ ምንጣጥሊት እያባረረችው ሄደና እና ወንዝ ተሻገረ፤ ከዚያ እርሷ ወንዝ ወሰዳት' ይሉህና 'መጀመሪያማ እንደዚያ አይደለም፤ እንዴት ተሻገርሽ ብሎ ጠየቃት' ይሉሃል።ይሄ ነው ቅርጹ፡፡ ሄደህ ታልፍና ተመልሰህ መጥተህ 'እንዴት እዚህ ደረሰ ?' ስትል 'እንዲህ የሆነው በዚህ መንገድ ስለሄዱ ነው' ብሎ በሚናገር መንገድ ነው ታሪኩን የተረኩት፡፡ እና ሕይወት ራሱ ሁሌ ቀጥተኛ አይደለም፡፡ ዛሬ ቁጭ ብለን ነገን እናስባለን፡፡ ነገ ላይ ሆነን ከአራት፣ ከአምስት ቀናት በፊት ወይም ከዓመታት በፊት የሆነን ነገር ነጋችንን ተጽእኖ እንደሚያሳድርበት እናስባለን፡፡ ስለዚህ እንደዚህ አይነት ሲኒማ ለምን አንሰራም የሚል ሃሳብ ነበረኝ፡፡ ትንሽ ይለይ ነበር" ሲል ሰውመሆን አጀማመሩን ይተርካል ፡፡

(በመጨረሻው ክፍል ከዚህ እንቀጥላለን)

ሻሎም ! አሜን×፫።

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹እጅ ካልቦዘነ ስሙኒም ባለውለታ ነች››

-የከተማ አርሶ አደር አረጋሽ ተመስገን

ጽጌረዳ ጫንያለው

**ግብርና ጤናዋም፣ ኑሮዋም እንደሆነ ታምናለች፡፡ በእርሱ ከህክምና ወጪ ሳይቀር ድናለች፡፡ በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎቿ ህመሟን አስታግሳለች፡፡ ልጆቿን ካለመመገብ ወደ መመገብ አሻግራለች፡፡ ጤናማ የሚሆኑበትን እድል ፈጥራም ለወግ ማእረግ እንድታበቃቸው ሆናለች፡፡ በግብርና ሥራዋ ሴሎችን ጤናማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ በተለይም ህጻናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ ቤት ተቀን መልፋቷ ያስደስታታል፡፡ እናም ግብርና ሕይወትም ገቢም ነው ትላለች የከተማ ገበሬዋ አረጋሽ ተመስገን፡፡**

**አገረጋሽ በዛ ቢባል ሁለት ሰዓት ብቻ ነው የምትተኛው፡፡ ሙሉ ጊዜዋን በግብርና ሥራ ላይ ታሳልፋለች፡፡ ጊዜው ደግሞ የትበረታታበትና በመንግሥትም ልዩ ትኩረት የተሰጠበት በመሆኑ ከከብት ርባታ አልፋ ዶሮ ማርባቱን ተያይዛዋለች፡፡ ንብ ማነብና አትክልትና ፍራፍሬ ማምረትም የተሰማራችበት ሙያ ነው፡፡ በዚህም ብዙዎች ብርቱዋ ሴት እያሉ ይጠሯታል፡፡ እኛም ይህቺን ብርቱ ሴት ብዙ የሚያስተምር የሕይወት ጉዞ አሳትና ልናስቃኛችሁ ወደድን፡፡**

## አባባ

አረጋሽ ተወልዳ ያደገችው በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ቢቸና ነው፡፡እናቷ የቤት እመቤት አባቷ ደግሞ በግብርና ሙያቸው የታወቁ አርሶአደር ናቸው፡፡ ይህ ነገር ደግሞ እርሷን በሁለት በኩል እየተሳለ እንዲህ አድርጓታል፡፡በእናት በኩል የቤት ውስጥ ሙያ መልመድ ሲሆን፤ በአባት በኩል ደግሞ ምርጥ አርሷደርነትን ነው፡፡በዚህም እድገቷ በሁለት መልኩ ውጤታማ ነበር፡፡ተወዳጅና ሁሉም የሚፈልጋት ልጅም ነበረች፡፡በዚህም ገና ጉልበቷ ሳይጠና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለች ነበር ለባል የተሰጠችው፡፡ ይህ ደግሞ ለተደጋጋሚ ችግር አጋልጧታል፡፡ ቤተሰቧን ትታ ጭምር ለስደትና እንግልት ዳርጓታል፡፡

የአረጋሽ ልጅነት ሲነሳ ሌላው የሚወሳው ነገር ብርቱ ሴት መሆኗ ሲሆን ከእናቷ ጋር የቤቱን ሥራ ከጨረሰች በኋላ ከአባቷ ጋር ደግሞ የግብርና ሥራው ላይ ትሰማራለች፡፡ ሁልጊዜ አለባበሷም ልክ እንደወንድ ቱታ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለሥራ የሚመቻት እርሱ ነው ብላ ታምናለች፡፡ በዚህም የእህቷ ልጅ ‹‹አባባ›› ይላት እንደነበር አይረሳትም፡፡ወንድሟም ቢሆን ከእርሷ የሚለይበት ነገር አልነበረም፡፡ምክንያቱ ደግሞ ወንድ ስለምትመስለው ነው፡፡ እናም ቅጽል ስሟ አባባ ነበር፡፡

በእርሻና በአረም ማንም የማይችላት ልጅ የነበረችው አረጋሽ፤ የትናንት መሰረቷ ለዛሬ ስኬት አብቅቷታል፡፡ለግብርና ያላት ፍቅርም ከፍ እያለ የመጣው ትናንት በተሰራባት ነገር ነው፡፡ጥቅሙንም ቢሆን በሚገባ ታውቀዋለች፡፡እናም ግብርናን ‹‹እንኳን ተማርኩት›› ትላለች፡፡

## ቀን እስኪያልፍ

አረጋሽ የትውልድ መንደሯ እጅግ አድርጋ ትወደው ነበር፡፡ በቤተሰብ መታገዝ ያለበት፣ በቤተሰብ መቀጣትና እድሜን እያወቁ ማደግ የሞላበት ነውና በዚያ መኖር ለእርሷ ልዩ ደስታን ይፈጥርላታል፡፡ ይሁን እንጂ ቤተሰቡ ያለ እድሜዋ ቢሆንም ለትዳር በቅተሻል በሚል በተደጋጋሚ ለጠየቀ ወንድ ሁሉ ይድሯት ነበር፡፡ይህ የሚሆነው ደግሞ ከአንዱ ቤት ጠፍታ ስትመጠጣ ማመላለስ ስለሚደክማቸው ነው፡፡እርሷም ብትሆን አንዱንም ተቀብላ አልተቀመጠችላቸውም፡፡

ለስድስት ሰዎች እንደተዳረች የምታስታውሰው አረጋሽ፤ ለመጥፋቷ ዋነኛ ምክንያት ልጅነት ስላለ ከሌሎች ሰዎች ጋር መላመድ አለመቻሏ ነው፡፡ ከቤተሰብ ተለይቶ ለያውም ራቅ ብሎ መኖር እጅግ ይከብዳል፡፡ ምርጫም መቀመጫም የባል ቤተሰቦች ብቻ ናቸው፡፡ ይህንን መቀበሉ ደግሞ ለእርሷ ቀላል አልሆነላትም፡፡ ስለዚህም እነርሱም ሆኑ እርሷ የሰለቻትን ተግባር በተደጋጋሚ አድርገዋለች፡፡ባስ ሲልባት ደግሞ የመጨረሻ ውሳኔ እንድትወስን ሆናለች፡፡ ይህም ቤተሰቧን ትቶ መጥፋትና የማያገኙዋት ቦታ መሄድ ፡፡

## በአስር ብር ደሞዝ ወደ አዲስ አበባ

የለመደችውንና የምትወደውን አካባቢ ትታ ወደማታውቀው ግን በዝና ወደሰማችው አዲስ አበባ ከተማ ለመሄድም አንድ አጋጣሚ አስወሰናት፡፡ ከመጨረሻውና ስድስተኛው የትዳር አጋሯ ጋር ጠፍታ በምትሄድበት ጊዜ ሰራተኛ የሚፈልግ አንድ ሰው አገኘች፡፡ይህ ሰውም በወቅቱ አስር ብር ሊከፍላት ተስማማና የት እንደሚሄዱ ነግሯት ወሰዳት፡፡ምንም የማታውቀውን ቦታ ለማየትም ቋምጣ ተነሳች፡፡ ቤተሰቧን እርግፍ አድርጋ ትታ መሸሸጊያዋን በዚህ ሰው ቤት ለማድረግ አምናው ተከተለችው፡፡

ሥራ አድክሟት የማታውቀው አረጋሽ በወቅቱ የገባችው አዲስ አበባ አልነበረም፡፡ ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ በሚገኘው ጫንጮ ከተማ ቢሆንም አልከፋትም፡፡ በገባችበት ቤትም ቤተሰባዊነት እየተሰማት ወራትን አሳለፈች፡፡ ቀጣሪዋ ከባለቤቱ ጋር ተጣልቶ የሚኖር ልጆቹን ብቻውን የሚያሳድግ በመሆኑ እናትም ሰራተኛም ሆና ቆየችው፡፡ ነገር ግን እያደር ባህሪው ተቀየረባት፡፡ መልካምነቷ አሸነፈውና የጠላችውን ትዳር አነሳባት፡፡‹‹ የልጆቼ እናት ሁኚልኝ፤ በጋብቻ እንተሳሰር›› አላት፡፡ ይህን ጊዜ እጅጉን አዘነች፡፡ ደስታዋ ጨለመ፡፡ ቤተሰቧን ያስተዋት፣ አካባቢዋን ያስለቀቃት ነገር እዚህም ተከትሏት መጣ፡፡እናም ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገባት፡፡

‹‹የጠሉት ይደርሳል ፣ የፈሩት ይወርሳል›› እንዲሉ አሁንም ከዚህ ቦታ መሰደድ እንዳለባት ወሰነች፡፡ ግን የት እንደምትሄድ አታውቅም፡፡አዲስ አበባን አለማወቋም ያናደዳት የዚህን ጊዜ ነው፡፡ግን ወደ አዲስ አበባ ከማምራት በስተቀር አማራጭ አልነበራትምና አደረገችው፡፡አዲስ አበባ የሰማቻትና በአዕምሮዋ የሳለቻት አይነት አይደለችም፡፡እንደገጠሩ ማህበረሰብ ቤት የእግዚአብሔር ነው አይባልባትም፡፡ ሰው በጎዳና ላይ ያድራል፡፡ ስለዚህም ከቤት ወጥታ ለማታውቀው አረጋሽ ሲኦል የገባች አይነት ስሜትን ፈጠረባት፡፡ለቀናትም በመንገድ ላይ አደረች፡፡በብዙ ተፈተነች፡፡

ከፈተናዎቿ የከፋው ደግሞ ማረፊያ ማጣቷ ሲሆን፤ማንን አነጋግራ ሥራ ማግኘት እንደምትችልም አለማወቋ ሌላው ችግር ነበር፡፡ ቆንጆና ወጣት በመሆኗ ደግሞ ደላሎች ይከተሏት ጀመር፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ላይ ሳለችም መልካም ከመሰላት ደላላ ጋር ተነጋግራ ግሮሰሪ ውስጥ በአስተናጋጅነት ተቀጠረች፡፡በእርግጥ ቀጣሪዋ ሥጋዋን ሸጣ ጭምር እንድታካፍላት የምትፈልግ ብትሆንም እርሷ ቁርጠኛ ነችና ያንን እንዳታስበው አድርጋት ተስማምታ ወደሥራ ገባች፡፡

ቀጣሪዋ ቃሏን አጥፋ ማታ ወጥተሽ ካልሰራሽ ማለት ጀመረች፡፡ከሦስት ሳምንት በላይ ግን በዚህ ቤት መቆየት አልቻለችም፡፡ ልትታገሳት ብትሞክርም ተደጋጋሚ ጥያቄዋ ግን በዚያ ለመቆየት አላስቻላትም፡፡እናም ‹‹ ይብቃኝ ደሞዜን ስጪኝና ልውጣ›› አለቻት፡፡ሴትዬዋ ግን ደሞዟን ብቻ ሳይሆን ልብሷን ጭምር ቀምታት አባረረቻት፡፡በሆነው ነገር እጅግ አዘነች፡፡በአንድ በኩል ደግሞ ተጽናናች፡፡ምክንያቱም ይህ ቤት የማታውቀውን የአዲስ አበባ ክፍል እንድታውቅበት አድርጓታል፡፡ከዚህ ቀጥሎም ማን ጋር ሄዳ ማነጋገርና መቀጠር እንዳለባት አሳውቋታል፡፡ ስለዚህ ዛሬ እንደዚህ ቀደሙ አትንገላታም፡፡ የፈለገችው ቦታ ተንቀሳቅሳ በፈለገችው ገንዘብ ትቀጠራለች፡፡

መኖሪያ ቤት በሰራተኝነት መግባት የመጀመሪያ ምርጫዋ ያደረገችውም ለዚህ ነበር፡፡ የገባችበት ቤት እጅግ መልካም ሰው ያገኘችበት ነበር፡፡ደመወዝ ግን የላትም፡፡እርሷ የፈለገችው ማደሪያ ቦታና የምትበላው ነገር በመሆኑ ይህ



ፎቶ፡- ሰጋፔ ጊዮን

ነገር በምትፈልገው ልክ ተሟልቶላታልና ደመወዙ አላሳሰባትም፡፡ነገር ግን እየዋለች እያደረች ስትሄድ መልካም ከሆነው አባወራ የሚደረግላት እንክብካቤ አክብሮት ባለቤቱን ሳያስደስታት ቀረ በዚህ ምክንያትም በረባ ባረባው ቁጣና ወቀሳ በዛ፡፡ አሁንም መልካሙን አባወራ አመስግና ወደሌላ የሕይወት አቅጣጫ ዞረች፡፡

የአረጋሽ ቀጣዩ መኖሪያ በልጅነቷ የተዳረ ችለት የባለቤቷ እናት ቤት ሆነ፡፡ እንደ እናት የሚንከባከባት ሰው በማግኘቷ አጋጣሚውን እጅግ ወደደችው፡፡የልጅነት ባሏ የነበረው ሰው ውትድርና ሄዶ በመሞቱ ብቻቸውን ናቸውና እርሷም ብትሆን እንደ ምትንከባከባቸው አምናለች፡፡ እርሳቸው ‹‹ከአንቺ ልጄ በረከት የሚሆን ፍሬ ባይኖረውም፤ የልጄ ማስረሻ ትሆኝኛለሽ›› ሲሏት እርሷ ደግሞ ‹‹ ትቼያቸው የመጣሁት ቤተሰቦቼ ምትክ ሁኑኝ›› በማለት ተደጋግፈው መኖሩን ተያያዙት፡፡ነገሮች በብዙ መልኩ የተለወጡበት ጊዜም ሆነ፡፡

## ሆድ ሳይጠና ...

ባለቤቷና እርሷ ከዚያ ቤት ሲወጡ ነብሰጡር ነበረች፡፡ሆኖም አብረው የቀጠሉበት ሁኔታ አልነበረምና የእርግዝናዋንም ሆነ የአራስነቷን ጊዜ ያሳለፈችው ብቻዋን ነው፡፡በብዙ ውጣውረድና ትግል ውስጥም ቆይታለች፡፡ለአብነት አዲስ ለምትመጣው ልጅ ብዙ መልፋትና የተሻለ ገቢ ማግኘት አለባትና ሌት ተቀን ትሰራለች፡፡ራሷን ለማረስም የሚያስፈልግ ነገር አለ፡፡እናም ዳግም ወደ ሥራ ሊያስገባት የሚያስችል ገንዘብ ማጠራቀም አለባት፡፡በዚህም መጀመሪያ ያላትን ገንዘብ ሰብሰብ በማድረግ ቤት ተከራየች፡፡ስፌት እየሰፋች ፤ ጥጥ እየፈተለች ልቃቂቱን መሸጡን ተያያዘችው፡፡ሆዷ እስኪገፋ ድረስም በተመላላሽነት ከስድስት በላይ ቤቶችን ይዛ እንጀራ ትጋግራለች፤ ልብስ ታጥባለች፤ ልጆችም ትንከባከባለች፡፡ ከፍ ሲል ደግሞ በራሷ እንጀራ እየጋገረች ትሸጣለች ፡፡ይህንን ሥራ ከወለደች በኋላም ቀጥላበታለች፡፡እንደውም ለ16 ዓመት ያህል በሥራው ላይ ቆይታለች፡፡

አረጋሽ ይህንን ሁሉ ብታደርግም ስትወልድ ግን ነገሮች ተመሰቃቀሉ፡፡አትረፊ ያላት ነፍስ ቤቱን ልቀቂ ተባለች፡፡የሚያርሳት በሌለበትና ራሷን በራሷ እያኖረች ስትታገል ሌላ ችግር መጣባት፡፡የት እንደምትገባም ግራ ገባት፡፡እናም አራስ ልጇን ይዛ ጎዳና ወጣች፡፡ግን እድል ከእርሷ ጋር ነበረችና የመሰረተ ትምህርት ተምረው የሚወጡ ሰዎች አገኟት፡፡በወቅቱ ባለሥልጣን የነበሩ ሰውም ችግሯን ጠየቋት፡፡አስረዳቻቸውና መፍትሄ ተፈለገላትም፡፡ጊዜያዊ መፍትሄው የራስ እምሩ ጥበቃ ቤትን መጠቀም ነበር፡፡በወቅቱ እራሷ ነበረች ያደረገችው፡፡ሰብራ ከገባች በኋላ ግን በባለሥልጣኑ ትግል ስምንት ዓመት እንድትኖርበት ሆናለች፡፡ከዚያ ስትወጣ ደግሞ አሁንም እድል ቀናትና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቤት ካሰራላቸው የተወሰኑ ሰዎች መካከል አንዷ ሆነች፡፡

## በር የሌለው ቤት

እርሷና ገና የተወለደችውን ልጇን ጎዳና ላይ ይዛ መኖር እጅግ አሰቃቂ ነበር፡፡ስለዚህም አማራጯን አንድ ነገር አደረገች፡፡ የራስ እምሩ የዘበኛ ቤትን ሰብራ መግባት፡፡ሰው ስላልነበረበት ለጊዜው ማንም ምንም አላላትም፡፡እየቆየ ሲሄድ ግን የደርግ መንግሥት ኢህአዴግን እየፈራ የመጣበት ወቅት ነበርና የአካባቢው ነዋሪ በዚያ መኖሯን ተቃረነ፡፡ቦታውን እንድትለቅ በተደጋጋሚ በቀበሌው ጭምር ተጠየቀች፡፡ገ ንዘብ አሰባስበው ወደ ቤተሰቧ ሊልኳት ፈለጉ፡፡ እርሷ ግን ከዚያ የወጣችበትን ምክንያት በሚገባ ታውቀዋለችና ዳግም ወደዚያ ጭንቀት ውስጥ መግባት አትችልም፡፡እናም ያልሞቱትን እናትና አባቷን ገላ ቤተሰብ እንደሌላት ተናገረች፡፡ ይህን ጊዜ ሰዎቹ ታገሷት፤ የመንግሥት አካላትም ተቀበሏት፡፡ በሸራ በር ሰርታ መኖሩን ተያያዘችው፡፡ከልጇ ጋር በዚያ ቤት ስምንት ዓመታትን ኖረች፡፡

ይህ ስምንት ዓመት ግን በእጥፍ ችግር የሞላ ነበር፡፡በር በሌለው ቤት ሴት ልጇን ማሳደግ ከባድ ሆኖባታል፡፡ ቀን ላይ ሥራ ከጨረሰች ለተወሰነ ደቂቃ ራሷን ካሳረፈች እንጂ ለልጇም ሆነ ለራሷ ስትል ብዙ ጊዜ እንቅልፍ በዓይና

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹እጅ ካልቦዘነ ስሙኒም...

ከገጽ 6 የዞረ

አይዞርም።አካባቢው በ12 ጥበቃ በፈረቃ ይጠበቅ ነበርና አንዱ ዘሎ ቢገባስ የሁልጊዜ ስጋቷ ነበር። በተጨማሪም በር ስለሌለው እብድና ሌባም ዘሎ መግባቱ እንደማይቀር ታስባለች። እናም አዳሯ ዘነዘና ይዛ ይነጋል። የሌሊቱ ጊዜ በመጠቀም እንጀራና ዳቦ ትጋግራለች።መጀመሪያ ተሸክማ ጉልት አስቀምጣ ትሸጥ ነበር።እየታወቀች ስትመጣ ደግሞ ፈላጊዎች ቤቷ ድረስ እየመጡ ይገዟት ጀመር።

‹‹ችግር ችግር ብቻ እንደሆነ አምነን ከተቀበልን መቼም አንለውጠውም።በዚያ ከመኖር በስተቀር አማራጭ እንደሌለን እናስባለን።ይህ ደግሞ ሕይወታችንን ከድጡ ወደማጡ ያደርገዋል›› የምትለው ባለታሪካችን፤ ለእርሷ ችግር ድህነቷን ማባረሪያ መንገድ ያየችበት ነው።መሥራትን የለመደችበትና አስተዋይነቷን ያበዛችበት ነው።በዓላማ ነው የተፈጠርኩት ብላ እንድታስብ አድርጓታልም።

ይህ ቤት ከችግር መውጫዋ መንገድ ሆነላት። ትዳርን በፍቅር እንድትቀበለው ያደረጋትም ነው።ፍራቻን ሸሽት ከአንድ የአካባቢዋ ነዋሪ ጋር ተዋወቀች።በራስ እምሩ ቤት የኖረችበትን ስቃይ እንዲያከትም አግዟታልም።ምክንያቱም የዛሬውን የልጆቿን አባት አግኝታበታለች። በመተጋገዝ ችግራቸውን አብረው እንዲወጡት እድል ሰጥቷታል።

### በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

ልጄ አደገችልኝ ብላ ሳትጨርስ ልክ አራት ዓመቷ ላይ ሌላ መከራ አገኛት።ነገሩ የተከሰተው በድርቁ ወቅት በ1977 ዓ.ም ነበር።እርሷ ግን እንጀራ እየጋገረች ለራሷ ተርፏት ጭምር ለሌሎች ትሸጥ የነበረ ቢሆንም መብላት ብቻውን ከህመም አያድንምና አብዝታ በመስራቷ እረፍት ባለማድረጓ ብሽሽቷ ላይ እንደ እባጭ ሆኖ በመውጣት ቢያማትም እውቀትና ግንዛቤው ስላልነበራት ወደሀኪም ቤት አልሄደችም።እያደር ግን ህመሙ አላንቀሳቅስ አላት።ወጥታ ገቢ ማግኘት እንኳን እንዳትችል አደረጋት።የዚህ ጊዜ ቁርጥ ሆነና ወደ ሀኪም ዘንድ ሄደች።ቁስሉ ወደ ካንሰርነት ተቀይሮ ነበርና የካንሰር ህመምተኛ እንደሆነች ተነገራት።

በወቅቱ በቀላሉ ለማመን የተቸገረች ቢሆንም ስር የሰደደ በመሆኑ አልጋ እንድትይዝ አደረጋት፤ ስራ አቁማም ትናንት ትታቸው የመጣችውን ቤተሰቦቿን ናፈቀች።ወደ እነርሱ ጋር ለመሄድም ተገደደች።እነሱም ያድናታል ብለው ያሰቡትን ሁሉ አደረጉላት።ሆኖም አንዱም ሊሳካ አልቻለም።ስለዚህም ሌላ አማራጭ መውሰድ እንዳለባት ገባት ።ወደ አዲስ አበባ ተመልሳም በቤተእምነት ደረጃ እንዲጸለይላት አደረገች አጋጣሚው ጥሩ ሆኖ ከህመሟ ተፈወሰች።

ከአንዱ ተላቀቅሁ ብላ ሳትጨርስ ሌላኛው ፈተና ይደረብባታል።አንዱ የግብርና ሥራን ከጀመረች በኋላ የገጠማት ትሰራበት በነበረው አካባቢ ከጎረቤቶች ጋር በነበረው አለመግባባት ለከብቶች ማደሪያ ያሰራችው በረት ፈረሰ በዚህ ምክንያት ደግሞ ላም ሞተችባት ። ይህም ‹‹የሞተ ላም ስጋ ስትሸጥ በአራዳ ክፍለከተማ 04 05 አግኝተን በቁጥጥር ስር አውለናል›› የሚል ነበር።ማንበብና መጻፍ ባትችልም ወዳጆቿ ብዙ ነበሩና የሰሙ ተሰብስበው መጡና ነገሩን አስረዷት።በዚህም እጅግ አዘነችና ጎረቤቶቿ በነገሯት መሰረት ነገሩ ውሸት መሆኑን ለማስረዳት ወደ ዜና አገልግሎት አመራች።ዜናውን በቃሏ ሸምድዳው ነበርና የተሳሳተ ዜና እንዳወጡባት አስረዳች።ዜናውንም እንዲሰረዝ አደረገች።

አረጋሽ ለፈተና የተፈጠረች ይመስል ነብሰጡር ሆና በር በሌለው ቤት ኖራለች።ብዙ ስቃይን አሳልፋለች።ከዚያ አረፍኩ ስትል ደግሞ በጥሩ ሁኔታ ተገንብቶ የተሰጣት ቤት በመፍረሱ



የቆሻሻ መከመሪያ የነበረ ቦታ ላይ እንድታርፍ ሆነች። ጎዳናውን አጽድታ መኖር፣ ልጆቿን ደስተኛ ማድረግ ይጠበቅባት ነበርና በብዙ ደከማለች።ቦታው በቀላሉ የሚጸዳ ባለመሆኑም ሽራ ወጥራ ወራትን አሳልፋለች።ልጆቿም ቢሆኑ በየጊዜው በምግብ እጥረት ይታመሙባት ነበር።

### ቤትን በራስ ጉልበት

ከ11 ዓመት ቆይታ በኋላ ጤና ጥበቃ የሰጣቸው ቤት በልማት ፈረሰ።በቀጥታ ዛሬ ወዳለችበት አካባቢም ሄደች።ባዶ መሬት የተሰጣት ሲሆን፤ ጫካ ሁሉ መንጥራ ነው በራሷ አቅም ቤቷን የሰራችው።ጫካውን ስትመነጥር በጥበብ ነበር።ምክንያቱም አጸዶቹ ለቤቱ ግርግዳ የሚሆንም አለባቸው።እናም ያንን አስተካክላ ጠርባ ቋሚና ወራጁን አዋቀረች።በኋላም ጭቃ አቡኩልኝ ለጥፉልኝና ለስኑልኝ ሳትል ረሷ አድርጋ ጨረሰች።የቆርቆሮ ማገርም ቢሆን መትታ ዝግጁ ማድረግ ቻለች።የቤቷን ውስጥ ሊሾም ራሷ አሳመረችው።አረጋሽ አሁንም ቢሆን ለከብት ማደሪያና መሰል ቤቶችን በግቢዋ ውስጥ መስራት ብትፈልግ ማንንም አትጠራም።

### የስሙኒ ውስታ

ነብሰጡር እያለች አንድም ቀን እረፍት አልነበራትም።ምንም በሆዷ እንዳልተሸከመ ሰው ተሯሩጣ ትሰራለች።አንዱ ስራዋ ደግሞ መርካቶ ሄዶ የወዳደቁ ድንችና ሽንኩርት እንዲሁም ቲማቲም ለቃቅመው ከሚሸጡት ላይ ገዝቶ ዳግም አትርፋ መሸጥ ነበር።ለአምስት ሳንቲም ትርፍ ሁሉ ደፋ ቀና ትላለች።ብዙ ጊዜ ስሙኒ ይዛ ነው ገበያው ላይ የምትገኘው።ሽጣ ወደቤቷ ስትገባ ግን ሃምሳ ሳንቲም ትሆናለች።ያተረፈቻትን 25 ሳንቲም ለአንዳንድ ነገር መገዛዢያ ታደርገዋለች።ይህ አይነት ንግዷ በዛ ከተባለ 75 ሳንቲም ድረስ ከፍ ይላል።‹‹ይህንን ያህል ሸክም በደረሰ እርግዝናዬ ላይ ተሸክሜ እየሄድኩ ለምን ይህችን ብቻ አተረፍኩ›› ብላ አታውቅም።በምታገኘው ትርፍ ሁልጊዜ ደስተኛ ናት።ወራት እየተቆጠሩ ሲሄዱ ደግሞ አመስጋኝነቷ ብሩን ጨመረው፤ብዙ ከሰራች ሻይና ዳቦ በልታና ጠጥታ ሁለት ብርና ሦስት ብር ወደቤቷ ይዛ ትገባለች።

ከመርካቶ ያመጣችውን ከጨረሰች በኋላም ቢሆን አረጋሽ ለራሷ እፎይታ አትሰጥም።ቆሎ በየጠጅ ቤቱ እየተዘዋወረች ለመሸጥ ትነሳለች።እነዚህና መሰል ሥራዎቿ የምታርፍበትንና ተረጋግታ የምትሸጥበትን እድል አመላክተዋታል።ይህም ቡና በኪሎ፣ ዘይት በሊትር ገዝታ ቡናውን በችርቻሮ መልክ በመለኪያ ዘይቱን ደግሞ በቡትሌ ትሸጣለች።ከሰል እያስመጣች መድባ በትንሹ ለሚገዙት ታቀርባለች።ስለዚህም ‹‹እጅ ካልቦዘነ ስሙኒም ባለውለታ ነች›› ብላ ታምናለች።‹‹ትልቅ ነገር መመኘት መልካም ቢሆንም ከፍተኛ ገንዘብ ሳገኝ ይህንን እሰራለሁ ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ግን ለድህነት ራስን አሳልፎ መስጠት ነው›› ትላለች።ትልቅ ገንዘብ ሳይሆን ትልቅ አዕምሮና የመስራት ፍላጎት እንደሚያስፈልግ ማመን ይገባል ባይ ናት።

"እኔ ስሙኒ ባለውለታዬ እንደሆነች የማምነው ያለምክንያት አይደለም። የለውጥ መሰረትን ጥላልኛለች። መስራት ከተቻለ ገንዘብ ጊዜውን ጠብቆ እንደሚመጣ አሳይታኛለች። ስለዚህም ትንሹን መናቅ ሳይሆን ማክበር ያስፈልጋል" ስትልም ትመክራለች።

### ያላትን ማካፈል

አረጋሽ ያላትን ማካፈል የምትወድ፣ ቤቷም ሰብስባ የምታሳድር ሰው ወዳድ ሴት ነች። ማንም ሰው ችግር ይፈጥርብኛ ብላ አታስብም።ቤት እንኳን ሳይኖራት የተቸገረ ካለ በተከራየችው ቤት ሳይቀር ሰዎችን መሰብሰብ ያስደስታታል። ዛሬም ቢሆን ይህ ባህርይዋ አብሯት ነው።በዚህም ‹‹ አታጣ ማርያም›› የሚል ስም አውጥተውላታል።ተግባቢነቷንና ተወዳጅነቷን በእጥፍ ጨምሮላታል። ብዙዎች እንዳይረሷትም ሆናለች።

### አረጋሽ ዛሬ

አረጋሽ ከሌሎች ሥራዎቿ ተላቃ ግብርናውን የጀመረችው ሲሲሰኤፍ የሚባል ግብረሰናይ ድርጅት በፈጠረላት የሥራ እድልና ገንዘብ አጠራቅማ በገዛቻት አንድ ላም ነበር።ጎረቤቶቿ በሚደፉት ውሃ ሳይቀር ትጠቀማለች።የእርሷም ፍሳሽ ቢሆን የተከለችውን አትክልት ያጠጣል እንጂ ግቢዋ ጥሶ የትም አይሄድም። ቆሻሻውንም አጠራቅማ ማዳበሪያ በመስራት ወደ ግልጋሎት ታስገባዋለች።በዚህም አሁን ጥሩ አርሶ አደር ሆናለች።በሌማት ቱሩፋት የተካተቱትን ሁሉ አሟልታ እየሰራች ትገኛለች። በርከት ያሉ ከብቶች አሏት።በዚህም የወተት ገቢ ታገኛለች።ዶሮ እርባታና ንብ ማነብም እንዲሁ ተግባራቶቿ ናቸው።በዚህም የምታገኘውን ገቢ ከፍ ታደርጋለች።ጓሮዋን በአትክልትና ፍራፍሬ ሞልታዋለችና ከራሷ አልፋ ለሌሎች ተርፋለች።

ይህና መሰል ጥንካሬዎቿ ደግሞ ለሁለተት ዓመታት ያህል ስራዋን ብታቆምም አሁንም ብዙዎች እንዳይረሷት የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ።አንዱ ትናንት ይገዟት የነበሩ ሰዎች ዛሬም ከእጇ ፍሬ ለመቋደስ ቤቷ ድረስ ይመጣሉ።

አረጋሽ ብርቱ ሰራተኛ በመሆኗ ከተለያዩ አካላት ሽልማትን ተቀብላለች።ለአብነት በከተማ ግብርና ብቻ በዓለም ላይ ካሉ የተለያዩ አደረጃጀቶች ሽልማት ተበርክቶላታል።በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም እንዲሁ በተደጋጋሚ ተሸልማለች።በግብርናው ዘርፍ አምባሳደር ነሽ የሚል የምስክር ወረቀትና ዋንጫም ተሰጥቷታል።

### መልዕክት

ሴቶች አገርን ማዳንም ሆነ መግደል ይችላሉ። ምክንያቱም ወላጆች ናቸው። ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ልጆች ማሳደግ፣ መንከባ ከብና በሥነምግባር ማሳደግ የሚችሉ። ስለዚህም ለአገራቸው ባለውለታ መሆን ከፈለጉ ለሁሉም ሥራቸው ፍቅር መስጠት አለባቸው። በተለይም እንደእኔ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩትና አገልግሎት የሚሰጡ አካላት አንድ ነገር እንዲያደርጉ እመክራለሁ። አትክልትና ፍራፍሬውን፣ እንቁላልና ወተቱን ሲያቀርቡ በንጽህና መሆን አለበት። ሰው እንዲድንበት፣ ጤናማ ሆኖ እንዲኖርበት ማድረግ መቻል ይኖርባቸዋል። ከሁሉም በላይ ወተት ላይ ምንም ነገር ባይጨምሩ መልካም ነው። ትርፍን በዚህ መልኩ ለማግኘት ማሰብ ነውር ስለሆነ። እናም ትርፋቸውን ለነብሳቸው አድርገው ጤናማ ትውልድ ላይ መስራት አለባቸው ።

# ፌስቲቫል ቱሪዝም- የኪነ ጥበቡ ድርሻ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኪነጥበብ ለአንድ አገር የቱሪዝም እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የቱባ ባህል ባለቤት ለሆኑ አገራት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት ከተሰራ ህብረተሰቡ ባህሉ፣ ወጉን፣ እሴቶቹንና ታሪኩን ጠብቆ ለትውልድ እንዲያስተላልፍ ከማድረጉም ባሻገር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ቱሪዝምን በመሳብ ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

በቅርቡ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ያዘጋጀው 14ኛው ከተማ አቀፍ የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል ለዚሁ አንድ ማሳያ ነው፡፡ ‹‹በሥነ ጥበባት ሕብራዊ መልክ የተዋበች ኢትዮጵያ›› በሚል መሪ ቃል ለሦስት ቀናት በተካሄደው የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል የተለያዩ የባህልና ኪነጥበብ ክንውኖች ተስተናግደዋል፡፡

ፌስቲቫሉ ቦታ ላይ ስንደርስ በተዘጋጁ ዱንኳኖች በስተቀኝ በኩል በአራት ማዕዘን በእያንዳንዳቸው ውስጥ በእጅጉ የተዋቡ የኢትዮጵያን ቱባ ባህል የሚያጎሉ ሥራዎች ተሰድረው ተቀም ጠዋል። የተለያዩ በጥንታዊና ዘመናዊ መልኩ የተዘጋጁ ባህላዊ አልበሳት ፣ ልዩ ልዩ ቅርሶች፣ የኪነጥበብ መሳሪያዎች፣ የእደ ጥበብ ውጤቶች በስፋት ቀርበዋል፡፡ በዚሁ ፌስቲቫል ላይ ሥራቸውን ይዘው ከቀረቡት አንጋፋ የኪነጥበብ ተቋማት ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ያሉ ተማሪዎች የተለያዩ ጥዑመ ዜማዎችን እያሰሙ ዝግጅቱን አጅበውታል፡፡ በተቃራኒው በኩል ባሉት ዱንኳኖች ደግሞ የተለያዩ የመጻህፍት፣ የቅርጻ ቅርጾችና የሥነ ጥበብ ውጤቶች (ስዕል) በስፋት ጎልተው የቀረቡበትን አውደ ርዕይ ተመልክተናል፡፡

በእጅጉ በተዋበ ህብረ ብሔራዊነትን በሚገልጽ መልኩ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን አልባሳትን ለብሰው ያጌጡ፣ በቡድን በቡድን ሆነው ህብረ ዝማሬን የሚያሰሙ የፌስቲቫሉ ተሳታፊዎች እንዲሁም ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ተማሪዎች የፌስቲቫሉ ድምቀት ነበሩ፡፡

ፌስቲቫሉ ሲጀመር በከተማዋ ያሉ የካበተ ልምድ ያላቸው የቴአትር ቤቶች የኢትዮጵያን ባህላዊ እና ዘመናዊ የኪነጥበብ ሥራዎች አቅርበዋል። የዳግማዊ ሚኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ማርሻል ባንድ ለየት ባለ ሁኔታ ልዩ የሆነ ጥዑመ ዜማ ያቀረበበት ያማረ ዝግጅትም ሌላው የዝግጅቱ ድምቀት ሆኗል፡፡

በዕይታዊ ጥበባት፣ በክንውን ጥበባት፣ በሥነ ፅሑፋዊ ጥበባት መስኮች የተለያዩ ሥራዎች የቀረቡ ሲሆን፤ የሥነ ጥበብ ተቋማት፣ ቴአትር ቤቶች፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤቶች፣ ከሁሉም ክፍለ ከተማ የተውጣጡ የኪነጥበብ ባለሙያዎች እና ሌሎችም ሥራዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡

በፌስቲቫሉ ላይ ዝግጅታቸውን ካቀረቡት አንጋፋ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ አገር ፍቅር ቴአትር ቤት አንዱ ነው፡፡ ቴአትር ቤቱ በርካታ ባህላዊና ዘመናዊ የሆኑ ኪነጥበባዊ ሥራዎች ይዞ መቅረቡን የሚናገሩት የቴአትር ቤቱ ስቴጅ ማናጀር አርቲስት ዮሐንስ አፈወርቅ ናቸው፡፡

እሳቸው እንደሚሉት ፤ የአገር ፍቅር ቴአትር ቤት ከተቋቋመበት 1934 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ የጥበብ ሥራዎች እያበረከተ ይገኛል፡፡ በፌስቲቫሉም ቴአትር ቤቱ እስካሁን ሲጠቀምባቸው የነበሩትን የኢትዮጵያን ባህል የሚያሳዩ ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት እንዲሁም ጥንታዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና በተለያዩ ወቅቶችን የሚያስታውሱ መገልገያ መሳሪያዎች ይዞ ቀርቧል፡፡

በተለይ በ1934 ተሰርቶ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረውን ‹‹እናት መሰንቆ›› በመባል የሚታወቀውን ለእይታ አቅርቧል፡፡ ይህ መሰንቆ ከሌሎች ለየት ባለ መልኩ የተሰራና በወቅቱ የማህበረሰቡ የፈጠራ ችሎታ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡



በፌስቲቫሉ ላይ ከቀረቡት መካከል ባህላዊ ትርኢቶች ይገኙበታል፣

በቴአትሩ ረገድ በአገር ፍቅር ቴአትር ቤት የተሰራው እነ ቀኝ ጌታ ዩፍታሄ ንጉሤ የነበሩበት ‹‹አፋጀሽኝ›› የተሰኘ እውቅ ቴአትር እና መሰል በርካታ ቴአትሮች የተዘጋጁባቸውን በአብዛኛው ባሕላዊ የሆኑ አልባሳትና መገልገያ መሳሪያዎች በማስተዋወቅ ትውልድ እንዲያውቃቸው ለማድረግ መቅረባቸውን ይገልጻሉ፡፡

በወቅቱ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ መገልገያ መሣሪያዎች በቴአትር ቤቱ እንደሚገኙ የሚናገሩት አርቲስት ዮሐንስ፤ አንጋፋዎቹ ቴአትሮች ከተሰሩባቸው አልባሳት በተጨማሪ አስቴር አወቀን የመሳሰሉ ድምጻውያን ለብሰውት ሲወዛወዙባቸው ከነበሩ አልባሳት እና መገልገያ መሳሪያዎች የተወሰኑት ለማሳያ ያህል በፌስቲቫሉ ላይ ማቅረባቸውንም ነው አርቲስት ዮሐንስ ያብራሩት፡፡

‹‹ይህ ፌስቲቫል በየዓመቱ የሚዘጋጀበትን ዓላማ በሚገልጽ መልኩ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ መጠን መሻሻሎችን እያሳየ፣ እየተለወጠና እያደገ የመጣ ነው›› የሚሉት አርቲስት ዮሐንስ፤ ቴአትር ቤቱ በእዚህ ፌስቲቫል ላይ የሚያደርገው ተሳትፎ እስካሁን ጠብቆ ያቆያቸውን እነዚህን ባህላዊ አልባሳት፣ መገልገያ መሳሪያዎችና የኪነጥበብ መሳሪያዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ህዝባዊ እይታዎች የሚያገኙበትና በኪነጥበብ ዘርፍም ያለውን ድርሻ የሚወጣበት ነው ብለዋል፡፡

አርቲስት ዮሐንስ ቴአትር ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ለአገር ፍቅር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ብዙ ሥራዎች መሥራቱን ነው የሚገልጹት። በተለይ በጥበቡ ዘርፍ አገር አንድ እንድትሆንና የከፍታ ማማ ላይ እንድትደርስ ለማድረግ በርካታ የኪነጥበብ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን አርቲስቱ ጠቁመዋል፡፡

የፌስቲቫሉ ተሳታፊ የሆኑት የኪነጥበብ ባለሙያው አርቲስት ጥላሁን ጉግሳ በበኩላቸው ከዚህ ፌስቲቫል የኢትዮጵያ ኪነጥበብ ያለበትን ደረጃ ለመገመት የሚያስችል ግንዛቤ ማግኘት መቻላቸውን ይናገራሉ፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፤ የኪነጥበብ ፌስቲቫሎች ዓመት ጠብቀው የሚዘጋጁ መሆን የለባቸውም፡፡ ሌሎች አገራት እንደሚያደርጉት በየወሩ፣ በየሦስት ወሩና በየስድስት ወሩ ሊቀርቡ የሚችሉበት ዝግጅት ቢሆን ይመረጣል፡፡ ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የሚጠቅሱት እንደዚህ አይነት በተደራጀ መልኩ የሚቀርብ የኪነጥበብ ፌስቲቫል ያለው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ነው፡፡

‹‹በፌስቲቫሉ የቀረቡት ዝግጅቶች የተወሰነ ቦታ ላይ ተገድበው የሚቀሩ ናቸው ብዬ አስባለሁ›› የሚሉት አርቲስት ጥላሁን፤ ዝግጅቶቹ ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን የሚያበረታቱ ከመሆናቸውም በላይ የውጭ አገር ቱሪስቶችን እንዲስቡና ገቢ እንዲያስገኙ ለማድረግ ድንበር ተሻጋሪ ሆነው ከአገር ውጭ መውጣት አለባቸው ሲሉ ያብራራሉ፡፡ ውጪ ለመውጣት አቅም እንዳላቸው ዝግጅቱ ጥሩ ማሳያ ነው ይላሉ፡፡

‹‹በመድረኩ ወጣቶቹ ያሳዩት ሞራል፣ ኃይል፣ ጉልበት፣ አቅም፣ ችሎታ፣ ብቃትና ፍላጎታቸው የሚደነቅ ነው›› ያሉት አርቲስት ጥላሁን፤ እንደዚህ አይነት ፌስቲቫሎች ላይ የሚጨመሩ ነገሮችን በማሳደግ በከተማ ብቻ ተገደቦ ያለውን የኪነጥበብ ፌስቲቫል ለዓለም እንዲደርስ ቢደረግ ኪነጥበብ ራሱን ከማሳደግ አልፎ ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ያስችላል በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

ሌላኛው የፌስቲቫሉ ተሳታፊ ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ደጀኔ እንደሚሉት ፤ ፌስቲቫሉ ኪነጥበብን ለማሳደግ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ በፌስቲቫሉ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ ሥራዎች ቀርበዋል፡፡ እንዲዚህ አይነት ፌስቲቫሎች ባሕል እንዲያድግና እንዲበለጽግ ያላቸው ፋይዳ ከፍ ያለ ስለሆነ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየስድስት ወሩ ቢዘጋጁ ጠቀሜታቸው ላቅ ያለ ነው፡፡

‹‹በኪነጥበብ ፌስቲቫሉ በየዓመቱ እካፈላለሁ፤ አሁንም እድሉ እንዳያመልጠኝ ሥራዬን ትቼ ነው የመጣሁት። ዝግጁቱም ከሚጠበቀው በላይ እየጨመረ መምጣቱን ተመልኬቻለሁ›› የሚሉት ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ፤ የኪነ ጥበብ ዝግጅቱ የአገርን ባህል፣ ወግን በመጠበቅ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችል መሆኑንም ይናገራሉ፡፡ ‹‹የተረሱ የኪነጥበብ መሣሪያዎች፣ ባሕላዊና ዘመናዊ የሆኑ አልባሳትና መገልገያ መሣሪያዎች ለትውልድ እንዲተላለፉ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

እንደ ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ገለጻ፤ በየዓመቱ ያለው ዝግጅት እየሰፋ፤ ይዘቱ እየጨመረ እና እየደመቀ መምጣቱ ለኪነ ጥበብ ምንያህል ትኩረት ተሰጥቶ ሥራዎች እንደተሰሩ ዝግጅቱ አንድ ማሳያ ነው፡፡ የኪነጥበብ ፌስቲቫሉ በአዲስ አበባ ብቻ ተወሰኖ መቅረት የለበትም፡፡ አጠናክሮ ማስቀጠል ከከተማ አቀፋዊነት ተሻግሮ አገር አቀፋዊ ሁነት እንዲሆን ከክልሎች ጋር ትስስር በመፍጠር የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ሁሉም በየተራ የሚዘጋጅበት ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡ በአገር አቀፍ መልኩ ሲዘጋጅ እርስ በእርስ ለማስተዋወቅ፤ ባሕልን ከባሕል ለማስተሳሰርም የሚያስችል በመሆኑ የባለሀብቱም ሆነ የሚመለከተው አካል ሁሉ ድጋፍ ቢያደርጉ ዘርፉን ማሳደግና ውጤታማ ማድረግ ይቻላል፡፡

ኪነጥበብ ለአገር ባለውለታ ነውና መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ ድጋፍ ማድረግ አለበት የሚሉት ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ፣ ‹‹የኪነጥበብ ዘርፉ አሁን ላይ የምናያቸው ነገሮች ተሻግረው መጪው ትውልድ ዘንድ እንዲደርሱ ማድረግ ይገባል›› ሲሉ ይገልጻሉ፤ ይህም ለአገር ፣ለልማት ፣ ባሕልና ወግን ለመጠበቅ ፣ ህብረተሰቡን ለማነቃቃት፣ ለማስተማር ግንዛቤን ለመፍጠር ትልቅ ፋይዳ አለው›› ይላሉ። በዘርፉ ጎልቶ እንዲወጣ ትኩረት ሰጥቶ ብዙ መሰራት አለበት የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡

በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ እንዳሉት፤ የባሕልና የኪነጥበባት ዘርፍ እጅግ በጣም ሰፊ የቱሪዝም ሀብት ማመንጫ እሴቶች ናቸው፡፡ የቱሪዝም ዘርፍን ለማስተዋወቅና ለቱሪስት መስህብ ከመሆን አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

የቱሪዝም ዘርፍን ለማሳደግ የሚቻለው የባህልና የኪነጥበብ ዘርፉ ካደገ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የባሕልና የኪነ ጥበብ ዘርፉን ለማሳደግ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ ‹‹የባሕልና የኪነ ጥበብ ዘርፉ የአገር ውስጥንም ሆነ የውጭ ቱሪስትን የሚስቡ፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል የፈጠሩ ናቸው፤ ማህበረሰቡ እየተዝናና ለአገሩ ኢኮኖሚ የራሱን አስተዋፅኦ የሚያደርግበት ነው›› ብለዋል፡፡

በተለይ በባሕልና ኪነጥበባት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ፌስቲቫል ማዘጋጀት ለብዙ ዜጎች የሥራ እድል ከማመቻቸት በተጨማሪ የፈጠራ ሥራን እንደሚያበረታታም አስታውቀዋል፡፡ ፌስቲቫሉ ባሕልንና የኪነ-ጥበባት ሥራዎችን ወደ ላቀ ደረጃ ከማሳደጉም በላይ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጠናከር እንዲሁም የቆየ ባህል፣ ታሪክና ልማድ ለትውልድ ለማሸጋገር ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

‹‹በኪነጥበብ ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ለሕዝብ የሚያቀርቡበት መድረክ ማመቻቸት ያስፈልጋል›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ፤እነዚህን ሥራዎች ከዚህም ባሻገር ከተማ አቀፍ፣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ በማስቻል ረገድ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሊያበረታታቸው፣ሊደግፋቸውና እውቅና ሊሰጣቸው እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ፌስቲቫል የኪነ ጥበቡ ማህበረሰብ ሥራዎቹን የሚቀርብበት አቅሙን የሚያሳይበት፣ የአገሪቱን ፣ የከተማዋን ገጽታ የሚገነባበት ለቱሪዝም ሀብት ማመንጫነት ሰፊ እድል የሚፈጥርበት ነው፡፡ ስለዚህ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት የኪነጥበብ ዘርፉን በማበረታታት ሊደግፉ ይገባል፡፡

‹‹ባህል፣ ኪነ ጥበባዊ ተግባራት እንዲሁም ታሪክ ለአገራችን ብርቅዬ ሀብቶች ናቸው›› ያሉት አቶ ስለሺ፤ በቀጣይም ባህልን፣ ታሪክንና ኪነ-ጥበባዊ ሥራዎችን መጠበቅና መንከባከብ ላይ መስራት እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ኪነጥበቡ አንዱ የቱሪዝም ሀብት ሆኖ ወደ ገበያ እንዲቀርብ እንደሚሰራ አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሰርፀ ፍሬስብሐት በበኩላቸው ፤ፌስቲቫሉ በከተማዋ ያሉትን የኪነ ጥበብ ሀብቶች አጉልቶ ለማሳየት የሚረዳ መሆኑን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የኪነ ጥበብ ወይም የሥነ ጥበብ ሥራዎች የእይታና የክዋኔ መድረክ ከማግኘት በላይ ቀዳሚ ጥያቄ የላቸውም፡፡ የሥነ ጥበብ ፈጠራ ትልቁ አንቀሳቃሽ ኃይል የህዝብ እይታ፣ አድናቆትና እውቂያ ማግኘት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነዚህ ዘርፉች ጎልተው የሚታዩባቸውን መድረኮች ማዘጋጀት በብዙ መልኩ አስፈላጊ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ትልቁ የቱሪዝም አቅም ያለው በማይስ ቱሪዝም በኩል ነው ያሉት አቶ ሰርፀ፤ ከማይስ ቱሪዝም መተግበሪያ መካከል አንደኛው የኪነ ጥበብ ፌስቲቫሎችን ደጋግሞ ማዘጋጀት የከተማዋን የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጠቅሰው ሲናገሩም፤ ከአዲስ አበባ ጋር ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው ዓለም አቀፍ ከተማዎች በከተሞቻቸው ዓመቱን ሙሉ መሰል ፌስቲቫሎች በማዘጋጀታቸው በርካታ የዓለም ሕዝብ ወደ ከተሞቻቸው እንዲጎርፍ በማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑም አስቻሏቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ይህንን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ በመውሰድ ደግማ ደጋግማ የኪነጥበብ ፌስቲቫሎች የማዘጋጀት የቤት ሥራ መውሰድ እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ ፌስቲቫሉች ካላቸው ማህበራዊ ጠቀሜታ ባሻገር እየፈጠሩ ያሉት አኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አቶ ሠርፀ የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል ከፍ ያለ የከተማዋ ኢኮኖሚ ሊያንቀሳቅስ የሚችል ሰፊ የእሴት ሰንስለት የሚነካ የሥራ እድል መስከ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ባህልና ኪነ ጥበብ ነክ ፌስቲቫሎች ከተማዋን ከማስተዋወቅና ከተማዋን ለቱሪዝም ተመራጭ ከማድረግ በተጨማሪ ለኢኮኖሚው ዘርፍ የጎላ ፋይዳ አለው ሲሉ ንግግራቸውን አሳርገዋል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የጀግናው ታሪክ በሮም አደባባይ

**ዋስልኝ አየለ**

የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክ በአገራቸው ብቻ የተወሰነ አይደለም።በጠላት አገር አደባባይ እንደ አንበሳ ሞገሳቸውን የሚያሳዩ ናቸው።ከ85 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው ጀግና ዘርዓይ ደረስ በጣሊያን ሮም አደባባይ የጣሊያንን ሕዝብ አፍ ያስያዘ የጀግንነት ገድል ፈጽሟል።በተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ የተጻፈው ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ - ከወልወል እስከ ጎንደር (ግንቦት 1927 - ኅዳር 1934)›› መጽሐፍ እና ሌሎች ሰነዶችን ዋቢ አድርገን በዛሬው የሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን ይህን ክስተት እንዘክራለን።

ዘርዓይ ደረስ የተወለደው በ1908 ዓ.ም ኤርትራ ውስጥ አዲ ሓይስ በተባለ ስፍራ ነው።ያደገው ደግሞ እዚያው ኤርትራ ውስጥ ሓዘጋ በተባለ ቦታ ነው።ርዕሰ ደብር እቁበ እንድርያስ (በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ትምህርት የተማሩና ያስተማሩ) በተባሉ የሃይማኖት አባት አማካኝነት የቤተ ክህነት ትምህርት ተምሯል።

ከቤተ ክህነት ትምህርት በኋላ ዘርዓይ አስመራ ከተማ ውስጥ በሚገኝና በሳልሳዊ ኢማኑኤል ስም በተሰየመ ትምህርት ቤት ገብቶ ዘመናዊ ትምህርት ተምሯል።ከዚያም መምህር ሆኖ ማስተማር ጀመረ።ይሁን እንጂ ዘርዓይ ለተማሪዎቹ ስለኢትዮጵያ ደጋግሞ መናገሩና መከራከሩ ለጣሊያኖቹ ምቾት የሚሰጥ ስላልነበር ከስራው ተባረረ።እርሱ ግን ‹‹ገብረሚካዜላውያን›› የሚባል ማኅበር አቋቁሞ ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ስለወደቀች ሁሉም ሰው በጸሎትም በመንፈስም ከኢትዮጵያውያን ጎን እንዲቆም መቀስቀስ ጀመረ።የኢትዮጵያን መወረር ተቃውሞ በጋዜጣ ላይ ገለፀ፡፡

ከአንድ የኤርትራ ገዢ ዘንድ ቀርቦ ሲጠየቅ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ጣሊያንኛና አረብኛ መናገር እንደሚችልና ኦሮምኛ፣ ሶማሊኛና አገውኛ የሚያስጠናው ቢያገኝ መማር እንደሚፈልግም ተናገረ።አገረ ገዢውም እንዲህ ዓይነቱን ሰው አስመራ ውስጥ ከማስቀመጥ ወደ ኢጣሊያ መላክ የተሻለ እንደሆነ በማመኑ፤ ዘርዓይ በመስከረም 1929 ዓ.ም ወደ ሮም ተላከ።በዚያም አንድ የቅኝ ግዛት አገር ዜጋ ሊያገኘው የሚገባው ከፍተኛ ደረጃ ተሰጥቶት የአስተርጓሚነት ስራውን ጀመረ።ይሁን እንጂ ያ ሁሉ ስጋዊ ምቾቱ ለኢትዮጵያ ነፃነት ከመታገል ሊያግደው አልቻለም፡፡

ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም የኢጣሊያ መንግሥት በዶጋሊ ጦርነት ለሞቱት ጣሊያናውያን የተሰናዳ የመታሰቢያ መርሃ ግብር በሮም ከተማ በአንድ የመንግሥት አደባባይ ላይ አዘጋጅቶ ነበር፡፡

ጥር 18 ቀን 1879 ዓ.ም የራስ አሉላ (አባ ነጋ) ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው የመጡትን ጣሊያኖችን ዶጋሊ በተባለ ቦታ ላይ ገጥሞ የጣሊያን ጦር አሰቃቂ ሽንፈት ገጥሞታል።ጣሊያን ለዚህ ክስተት ነበር መታሰቢያ ያዘጋጀች።

ዘርዓይ በዕለቱ ፒያሳ ዲ ፒአሞንቴ በተባለው አደባባይ እንዲገኝ የተደረገው የኢትዮጵያን የጦርና ሌሎች ዕቃዎች ይዞ ለማሳገጫነት እንዲቆም ነበር።ዘርዓይ ከያዛቸው እቃዎች መካከል አንዱ ራስ አሉላ ዶጋሊ ላይ ጀብዱ የሰሩበትና በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ከኢትዮጵያ ተዘርፎ የተወሰደው ጎራዴ ነበር።ዘርዓይም እቃዎቹን ይዞ እንዲሄድ ከመታዘዙ በቀር ለመሳለቂያነት መቆም እንዳለበት አልተነገረውም ነበር።

ዘርዓይ ፒያሳ ዲ ፒአሞንቴ አደባባይ ሲደርስ እንግዳ ነገር ተመለከተ።ቀደም ሲል አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተተክሎ የነበረው የይሁዳ አንበሳ ሐውልት ሮም አደባባይ ላይ ተተክሎ አየው።ከሐውልቱ ላይ ሁለት ግልገሎች የምታጠባ የተኩላ ምስል ተቀምጦበታል።በአንበሳው መስቀል ላይ ደግሞ የኢጣሊያ ባንዲራ ተሰቅሏል።የኢትዮያ ሰንደቅ ዓላማ መሬት ላይ ተጥሏል።በዙሪያው ተጽፈው ከሚታዩና የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ክብር ከሚነኩ መፈክሮች መካከል አንዱ ‹‹ ... የይሁዳ አንበሳን ልጆችሽ እንደፍየል ጭራውን ጠምዝዘው አምጥተው ከእግርሽ ስር ያሰግዱታል ...›› የሚል ነበር።በአደባባዩ የተሰበሰበው ሕዝብም እየሳቀና እየጮኸ አንበሳው ላይ ምራቁን በመትፋት ያፌዝና ይሳለቅ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ ሁኔታውን በመገረምና በመናደድ




ስሜት ሲመለከት ማርሻል ማሪዮ ኢሶን የተባለ የዘበኞች አለቃ ወደ ዘርዓይ ቀርቦ ድርጊቱን መመልከት እንደማይችል ነገረው።በተጨማሪም ማርሻል ኢሶን የዘርዓይን መናደድ ስለተመለከተ ዘርዓይን ከአካባቢው ሊያባርረው ሞከረ።ዘርዓይ ‹‹እናንተ የምታዩትን እኔ የማላይበት ምን ምክንያት አለ?!›› ብሎ ጠየቀው።የዘበኞቹ አለቃም የዘርዓይን ጥያቄ እንደድፍረት በመቁጠር ‹‹ ... ከእንግዲህ አንበሳ የለም! ለተኩላዋ ልትሰግድና ልታመልካት ይገባሃል!›› አለው። ዘርዓይ ግን ‹‹አይደረግም!›› አለ።ክርክሩ ከረረ። ማርሻል ኢሶን ‹‹ ... ከእንግዲህ በኋላ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ልነግርህ እወዳለሁ ... ያውም ንጽሕናውን ያሻሽል እንደሆነ ... ›› አለ።ዘርዓይ በእልህ ተከራከረ።አንበሳው ጣሊያኖችን ከአንድም ሁለት ጊዜ ሰባብሮ ድራሻቸውን እንዳጠፋቸው አስረዳው።የዘበኞቹ አለቃ ‹‹ ... ከአንበሳው ጀርባ ላይ ወጥታችሁ አሳዩት ቁርጡን ይወቀው!›› የሚል ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ሰጠ።ሕዝቡ ጭምር አንበሳው ላይ ለመውጣት ተተረማመሰ።

ዘርዓይ ደረስ ሥራውን የጀመረው በዚህ ሰዓት ነበር።በያዘው ጎራዴ ጣሊያኖችን መጨፍጨፍ ጀመረ።‹‹ ... ከእንግዲህ በኋላ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ማመን አለብህ ... ተኩላዋን ልታመልካት ይገባሃል ...›› ብሎ ያፌዘበትን ማርሻል ኢሶንን ለአንበሳው እንዲሰግድ አድርጎ እጅና እግሩን ክፉኛ አቆሰለው።የሌሎችንም ሬሳ በአንበሳው ስር ጎተተው።ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ እንኳ ለመሸሽ አልፈለገም።

ሮም ተሸበረች።‹‹ኢትዮጵያ ሰብራ ገብታ የኢጣሊያን ሕዝብ ጨፈጨፈችው ... ታጥቀህ ራስህን ተከላከል ...›› ተብሎ ታወጀ።

ሁሉም በያለበት ተኩስ ከፈተ።በዘርዓይ ጎራዴና በአደባባዩ ላይ በነበረው ትርምስ ምክንያ ከሞተው ሰው በተጨማሪ ‹‹ ... ታጥቀህ ራስህን ተከላከል ...›› ተብሎ በታወጀው አዋጅ ምክንያት ብዙ ሰው እርስ በእርሱ ተጋደለ።የኢጣሊያ መንግሥት ባለሥልጣናት ድርጊቱ ውርደት ስለሆነባቸውና ነገሩን በምስጢር ስለያዙት ስንት ሰው እንደሞተ በውል አይታወቅም።አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች በዕለቱ በጥቂቱ የአምስት ሰዎች አስክሬን ከአደባባዩ ላይ መነሳቱን ሲጽፉ ሌሎች ደግሞ ቁጥሩን እስከ 18 ያደርሱታል።በትርምሱ ምክንያት ብዙ ሰዎች መቁሰላቸው የታሪክ ጸሐፊዎቹን አስማምቷል፡፡

ዘርዓይ ጣሊያኖች ላይ እርምጃ መውሰድ የጀመረው ከረፋዱ አራት ሰዓት አካባቢ ነበር።ሽብሩ ግን እስከ 10 ሰዓት ተኩል ድረስ ቀጥሎ ነበር።ከቀኑ 10 ሰዓት ተኩል አካባቢ አገሪቱ ሰላም መሆኗንና ሽብሩ የተፈጠረው አንድ የአዕምሮ በሽተኛ ህመሙ ተነስቶበት እንደሆነ የሚገልፅ አዋጅ ተነገረ።የአዋጁ ቃል ይህ ብቻ አልነበረም።‹‹ ... ወደ ፒያሳ ሄዳችሁ እጁን ያዙ!›› የሚል ትዕዛዝም ነበረው።በዚህ ትዕዛዝ ምክንያት የከተማው ሕዝብ እንደገና ወደ አደባባዩ ወጣ።

ዘርዓይ ደረስ ሰውነቱ እንደነብር ተቆጣ።በተኩላዋ ሐውልት ላይ ቆሞ በመናገር ሕዝቡን ዝም አሰኘው።‹‹ ... በየቤታችሁ እየዞርኩ ብዙ ሰው አርድ ነበር።ግን እኔን አስሮ የያዘኝና እዚህ ሲያኮራምተኝ የዋለው የአንበሳው ፍቅር ነው።ደግሞም አሟሟቴ ከአንበሳው ስር እንዲሆንልኝ ፈልጌ ነው።ወንድ ይምጣና ይማርከኝ ...›› ብሎ ተናገረ።ከተኩላዋ ላይ ወርዶ አንበሳውን እየዳሰሰ ቆመ።

አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ ወታደሮች በሞተር ሳይክል፣ ከሁለት አቅጣጫ በመምጣት ዘርዓይን ተኩሰው መቱት።ጎራዴውን መዘዘና እንደገና ወደ ሕዝቡ ገሰገሰ።ከተማዋ በተኩሱና በሽሽቱ ምክንያት እንደገና ተረበሸች።ዘርዓይ ቢወድቅም ሊቀርበው የደፈረ ሰው አልነበረም።ጎራዴውን ይዞ ከወደቀበት ተነሳ።መሬት ላይ ወድቆ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማንሳት በደሙ ለውሶ አንበሳው ላይ ሰቀለው።ተኩላዋ ላይ የነበረውን የኢጣሊያ ባንዲራ የተሰበሰበው ሕዝብ እያየው አወረደው፤ ቀዳዶ ከመሬት ጣለውና ረገጠው።አንበሳውን እየሳመ ያነጋግረው ነበር።ዘርዓይ ይህ ሁሉ ሲያደርግ ሊያስቆመው የሞከረ ሰው አልነበረም።አሁን ግን ወታደሮቹ ደግመው ተኮሱበት።ዘርዓይም ወደቀ ግን አልሞተም ነበር።

ዘርዓይ ይህን ሁሉ ሰርቶ፤ በስድስት ጥይት ተመትቶ መትረፉ ጣሊያኖችን አበሳጫቸው፤ አስደነገጣቸውም።በወቅቱ በሮም ከተማ ውስጥ ከነበሩት ሐኪም ቤቶች ሁሉ የተሻለ ወደሚባለው የሕክምና ተቋም (ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ፖሊክሊኒክ) አስገቡትና ሕክምና ተደርጎለት አገገመ።ሐምሌ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ቤኒቶ ሙሶሊኒ በዘርዓይ ጥቃት የቆሰሉትን ለመጠየቅ ሐኪም ቤት ሲደርስ ማርሻል ማሪዮ ኢሶን ሞቶ እየተገነዘ ነበር።ለኢሶን ያመጣለትን ኒሻን አስቀምጦ በከፍተኛ ቁጣ ዘርዓ ወደተኛበት ክፍል ገባ።አገግሞ ስላገኘው የበለጠ ተናደደ። ‹‹ ... አንተ ነህ ሮምን የደፈርካት?›› ብሎ ጠየቀው።ሙሶሊኒም ዘርዓይ በሚገባ ታክሞ እንዲድን ለሐኪሞቹ አደራውን ሰጠ።ዘርዓይን በሞት መቅጣት የኢጣሊያን ስም በማይረባ ነገር በመላው ዓለም መበተን መሆኑን ገልፆ፤ በዳነ ጊዜ በቃልም በጽሑፍም ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ የአዕምሮ ሕመምተኛ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ እንዲዘጋጅና ዘርዓይም ሕመምተኛ መሆኑን እንዲያምን እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጠ።

ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የተባለው ሐኪም የሙሶሊኒን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ላይ ታች አለ።ለብዙ ቀናት አግባብቶ አንድ ወረቀት እንዲፈርም አቀረበለት።ደብዳቤው ስለተደረገለት ሕክምና አመስግኖ ‹‹ በ500 ወታደሮች አደባባይ ላይ በድንገት ታምሜ በሰዎች ሕይወት ላይ ስላደረስኩት በደል ይቅርታ እጠይቃለሁ።በስድስት ጥይቶች የተመታው ሰውነቴና አንጎሌም ድኖ በቅርብ ቀን ለመውጣት ሀኪሙ ተስፋ ሰጥቶኛል ...›› የሚሉ ሃሳቦችን ያካተተ ነበር።ዘርዓይ ደብዳቤውን ከሐኪሙ ነጥቆ በመቀዳደድ ፊቱ ላይ በተነበት።ቀደም ሲል ስለዚሁ ጉዳይ በተደረገ ክርክር ላይ ዘርዓይ ‹‹ ... በእናንተ አፍ እውነት የሚነገረው መቼ ይሆን?›› ብሎ በድፍረት የጠየቀው ፕሮፌሰር ኮንስታንቲኒ የሐፍረት ማቅ ለብሶ ወጣ፤ድጋሚ ወደ ዘርዓይ አልተመለሰም፡፡

ፕሮፌሰር ኮንስታንቲኒ በድጋሚ እርሱ በአካል ወደ ዘርዓይ ባይመለስም ጥረቱን ግን አላቋረጠም ነበር።ሁለት ኢትዮጵያውያንን (አንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ ደጃዝማችና አንድ መነኩሴ) ላከበት።ሁለቱ ሰዎች የዘርዓይን አቋም ለማስለወጥ ብዙ ደከሙ።የኢጣሊያን መንግሥት ኃያልነትና የእርሱን ወጣትነት እያገናዘቡ ብዙ አባበሉት።እርሱ ግን ሃሳቡን መለወጥ አልፈለገም።ወደ ደጃዝማቹም ዞሮ ‹‹ ... እንደርስዎ ያለ ሰው የማንም ጭነት ማጓጓዣ መሆን አልነበረበትም›› አላቸው።በተጨማሪም ‹‹ ለእነርሱ ክብርና ለእነርሱ ወረራና መስፋፋት ከቶ የእናንተ አጠንጣኝነት ምንድን ነው? ሲል ጠየቃቸው።ደጃዝማቹ ግን መልስ አልነበራቸውም።ዘርዓይ ቀጥሎም ‹‹እንስሶች እንኳ ጌታቸውን ይወዳሉ።እናንተ ግን ቅሌታችሁን ተሸክማችሁ ትዞራላችሁ!›› ብሏቸው ወደ መነኩሴው ዞረ።‹‹የእግዚአብሔር እንደራሴ መስለው በጥቁር ጨርቅ ትምነሸነሻላችሁ። የሰውን የእኩልነት ኑሮ ለማጥፋት ከላይ ተልካችሁ የመጣችሁ መውሰፍቶች ናችሁ! ቅስናዎን ይተውት! ተራ መሐይም መስለው እንደሌሎች ባንዳዎች ቢያገለግሉ ይሻላል፤ ከአጠገቤ ውጡ!›› ብሎ አባረራቸው።ዘርዓይ አቋሙን እንደማይቀይር ስለታወቀ በድጋሚ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አልቀረበለትም፡፡

አንድ ጊዜ መደበኛ ፍርድ ቤት ሌላ ጊዜ የጦር ፍርድ ቤት ሲያመላልሱት ቆይተው ታሰረ፤ በዚያው በእስር ቤት እያለ በ1937 ዓ.ም ሕይወቱ አለፈ።አስክሬኑም ወደ ኤርትራ መጥቶ በሐዘጋ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደርጓል፡፡

እነሆ ይህን ጀግና ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ባህታዊው ባለቅኔ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



‹‹ኢትዮጵያዊው ሼክስፒር›› ይለዋል ጉምቱው ደራሲ ስብሐት ገብረእግዚያሔር ወዳጁ ስለነበረው ባለቅኔው ሙሉጌታ ተስፋዬ ወይንም አያ ሙሌ ሲናገር፡፡

የአያ ሙሌ የሕይወት መንገድ እጅግ በጣም ረዥም ነው። እንደ ምድር ባቡር ከንፈው እንደ ሰማይ አሞራ ቢበሩም የእርሱን የኑሮ ግዛት ተናግረው አያገባድዱትም። ለመድረስም ሆነ ደርሶ ለመያዝ ያዳግታል፣ ምክንያቱም ስራዎቹ ብቻ ሳይሆኑ እርሱ እራሱ ቅኔ የነበረ ሰው ነውና፡፡

ከአባቱ ከአለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን እና ከእናቱ ከወይዘሮ ታጋይ ንጋቱ ሚያዚያ 18 1946 ዓ.ም በወሎ ጠቅላይ ግዛት በወልዲያ ከተማ ነበር የተወለደው። የ1ኛ ደረጃ ትምህርቱን በእቴጌ ጣይቱ ትምህርት ቤት ተማረ። በወልዲያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ደግሞ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን ቀጠለ። አያ ሙሌ ስለ አስተዳደጉ ብዙ ተናግሯል። “የድሃ ልጅ ነኝ። እናቴ እጄን ይዛ ትምህርት ቤት ያስገባችኝን ቀን እንጂ የገዛችልኝ ደብተርና እስክሪፕቶ ትዝ አይለኝም። ያደኩትም በውጣውረድ ነው” ይላል ልጅነቱን በአንድ ወቅት ሲያስታውስ፡፡ የልጅነት ሕይወቱን የገፋው እንደ አብዛኛው ልጅ ከቤተሰቦቹ ጥላ ስር ሆኖ አልነበረም። ያደገው ከአያቱ ጋር ቢሆንም ምንም የማድረግ አቅም ስላልነበራቸው የኑሮን ፈተና በራሱ ሊጋፈጣት ግድ አለው። ሊስትሮ ሆኖ ጫማ በመጥረግ እንዲሁም ቱሪስቶችን የማስጎብኘት ስራም ይሰራ ነበር። ከወዛደርነት ጀምሮ ያልሞከራቸው የሥራ አይነቶች የሉም። ሊስትሮ እየሰራ በነበረበት ወቅት የደንበኛውን ሱሪ በቀለም አበላሽቶ የቀመሳት ኩርኩም ጊዜው አልፎም ‹‹ታመኛለች›› ይል ነበር።

የግጥም ስብስቦቹም ሆኑ የሙዚቃ ሥራዎቹ እያደር እንደ ወይን እየጣፈጡ የሚሄዱ ናቸው። ቅኔዎቹን ከየትም አያመጣቸውም። ስለምን ልጻፍ እያለም አይጨነቅም። ሁሉንም ከሕይወቱ እየጨለፈ ይቀዳቸዋል። ከ30 ዓመታት በፊት የሰራቸው የሙዚቃ ግጥሞች ዛሬም ድረስ እንደ አዲስ ይደመጣሉ። ብጽዓት ስዩም በእንባ ታጅባ ‹‹አደራ ልጄን አደራ›› እያለች ስታዜም ብዙዎች በእንባ ተራጭተዋል። ሃና ሸንቁጤና ኩኩ ሰብስቤን ጨምሮ ለበርካታ እውቅ ድምጻውያን የሰራቸው የሙዚቃ ግጥሞች ከጆሮ በላይ ልብን የሚያረሰርሱ ናቸው። በርካቶችን ከዝና ማማ ላይ ሰቅሎ እርሱ ግን የጉስቁልና ኑሮ እጣፋንታው ሆነ። ከስሥራዎቹ ሁሉ አንደኛው ግን እንዲሁ እንደዋዛ ተናግሮ ለማለፍ የማይቻል ነው። አያ ሙሌ እራሱ ይህንን ስራ ‹‹ልክ እንደልጄ ነው›› ይለዋል። ወፍዬ.. ወፊቱ ድምፃዊ አበበ ተካ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ላይወጣ ከሕዝብ ልብ ውስጥ ገብቶ የቀረበት ስራ ነው። ለዘመናት ደግመን ደጋግመን ብንሰማውም የሙዚቃው ውበት ሊደበዝዝ፣ ቅኔውም ሊረግፍ አልቻለም። የሙዚቃውን ሙሉ ግጥም ለማስፈር ባይቻልም እስቲ ገሚሱን እንኳን እንመልከት።

**....ጭራ ጭራ የምታድረው**
**ጭራ ለቅማ የምታድረው**
**እንዴት አስናቀችኝ**
**ቀድማኝ ጎጆ ወጥታ ጎጆ አስተማረችኝ**

**........**

**ገመና ከታቹን የሳር ቤት ያማረሽ**
**ሚስጥረ መስኮት ማነው ያስተማረሽ**
**ካፈር ክዳን ጎጆ መሬቱን ፈልፍሎ**
**ከሰማይ ቤት እጣሽ ማን በሰጠኝ ከፍሎ**

**.....**

**ፈጣሪዋን አምና ያፏን ጥሬ ሰጥታ**
**ለጭሮ አዳር ውሎ በዝማሬ ወጥታ**
**አዳኝ እንዴት ያጥቃት ፍርድና ዳኛ አጥታ**
**አጣው ነጣው ብሳ እንደሰው ባይከፋት**
**ምፅዋት ባትለምን ተርፎን ባንደግፋት**
**ጎጆዋ ለቻላት ምን ነበር ባንገፋት**

**.........**

**ታማ ትንፋሽ አጥሯት ደክማ ስታጣጥር**
**ማን ያቃናት ይሆን ውስታ ሳይቆጥር**
**ወልዶ ማሳደጉን ብዙ ሰው ቢያውቅበት**
**ያፋን ማን ይሰጣል የጁ ሲርቅበት**

*እህህ ወፊቱ እሁሁ ወፊቱ እህህ ወፍዬ እህህ ወፊቱ*
*እህህ ወፊቱ...*

በዚህ የሙዚቃ ግጥም ያፉን ማን ይሰጣል የእጁ ሲርቅበት እያለ ወፊቱ ለልጇ የምትከፍለውን መስዋዕትነት ይገልጸዋል። ሙዚቃውን ልብ ብለን ካደመጥነው ግን በሙዚቃው ውስጥ ያስቀመጠው ቅኔያዊ ሃሳብ ምን ያህል ጥልቅና በቀላሉ የማንረዳው እንደሆነ እናያለን። ከወፊቱ ውስጥ የሚገኘው ምስል ቃላትም ሆነ ብሩሽና ሸራ ሊገልጡት የሚችሉት አይደለም። ይህ ስራ የምናቡ ርቀት ምን ያህል እንደሆነ ያሳየናል። በ1977 ዓ/ም በሃገራችን ድርቅ በተከሰተበት ወቅት አያ ሙሌ ለፈጣሪው 'ከመንበርህ የለህማ' እያለ ክርር ባለ ስሜት የጻፈው የግጥም ስራው ዛሬም ድረስ ከብዙዎች አዕምሮና ልብ ውስጥ አለ፡፡ እነዚህን ለአብነት አነሳን እንጂ የእርሱ ሥራዎች ለቁጥር የሚታክቱ ወሰን አልባ የጥበብ ድንበር ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ አያ ሙሌ ከአማርኛ ውጭ ትግርኛ፣ ግዕዝ፤ አፋርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ አረብኛ፣ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ አቀላጥፎ ይናገራል፡፡ ቅኔ የሚዘርፈው በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በእንግሊዝኛውም የሚጽፋቸው ግጥሞች የእውነትም የሼክስፒር እንጂ የአንድ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ አይመስሉም።

ጠቢቡ ባለቅኔና ሕይወቱ ግን የአንዲት ምድር ሁለት ዳርቻ ናቸው። ከባለሥልጣናት እስከ ቱጃሩ የጥበብ ሰዎችን ጨምሮ ከሊቅ እስከ ደቂቁ በቅርበት የሚያውቃቸውና የሚያውቁት በርካታ ሰዎች እያሉ እርሱ ግን በብቸኝነት ዓለም ከርታታ ባህታዊ ሆኖ ምንም እንደሌለው ሰው ከጎዳና እስከ ገዳማት ሲናውዝ ነበር የሚኖረው። ስላጣ ነው ብለን እንዳንል በሙዚቃ ሥራዎች ያገኘውን ገንዘብ እንኳን ለራሱ ሳይሆን ለድሆች ነው የሚያድለው። ምናልባት ወፈፍ ቢያደርገው ነው ብለን እንዳንፈርድ ደግሞ እራሱን ከመጉዳቱ ውጭ ፍጹም ከዚህ የተለየ ሰው ነው። አያ ሙሌ እያበሳጨ የሚያስቀን፣ እያናደደ የሚያስለቅሰን በሁለት የተለያዩ ስሜቶች ግራ የሚያጋባን እርሱ እራሱ ቅኔ የሆነ ሰው ነው። ስለ ሃይማኖት ሲያወራ አንዴ ዳዊት የደገመ ቄስ፣ ሌላ ጊዜ ሃዲስና ቁርአን የቀራ ሼህ ሆኖ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ነብይም ይቃጣዋል፡፡ ይሆናሉ የሚላቸው ብዙ ነገሮች ሆነው እንደሚገኙ የቅርብ ወዳጆቹ ይመሰክራሉ።

አደላድሎ የሚያኖረውን የሥራ እድል ቢያገኝም እሱ ግን አልሆንልህ እያለው ሥራውን እየለቀቀ የነብሱን ጥሪ ፍለጋ ይሄዳል። በአንድ ወቅት በተራድኦ ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ ደሞዝ ተቀጥሮ በመሥራት ላይ ሳለ ለሥራ ወጣ ወዳለ አካባቢ ሄዶ የህጻናቱን ራብ በመመልከት በዚያው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ፡፡ ሥራውን ጥሎ ለረዥም ጊዜ ወዴት እደተሰወረ አውቃለሁ የሚል ሰው ጠፋ። እርሱ ግን ምንም ነገር ላለማየትና ላለመስማት ወደ ገዳም ገብቶ ነበር፡፡ በታዋቂ ጋዜጣና መጽሄቶች ላይ በጋዜጠኝነት እየሰራም በመሃል መልሶ ይተወዋል። ባህታዊ ይሆንና ድንገት ከነበረበት የሕይወት ዘይቤ አፈንግጦ ይወጣል።

የአያ ሙሌ ገጠመኞችና የኑሮ ሰበዞች አያሌ ናቸው። ጊዜው አበበ ተካ በሙዚቃው የነገሰበት ወቅት ነበር። አያ ሙሌ ደግሞ ሥራ አስኪያጁ። አንድ ጊዜ ወደ ጎንደር ለስራ ሄደው ለብቻው ከአስፋልት ዳር እየተጓዘ ሳለ ብዙ የተቸገሩ ሰዎች ተሰብስበው ይመለከታል። እናም አያሙሌ ሁሉንም ጠርቶ በዙሪያው ሰበሰባቸውና ከኪሱ የነበረውን እረብጣ ብር እያወጣ ማደል ጀመረ። ይህን የተመለከተው ፖሊስም በነገሩ ተጠራጥሮ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዞት ሄደ። ደግነቱና ለሰው አዛኝነቱ በእጅጉ የተለየ ነበር፡፡ ተቸግሮ በባዶ እግሩ የሚሄድ ሰው የተመለከተ እንደሆን የእግሩን ጫማ አውልቆ ይሰጥ ነበር፡፡ ለራሱ ቁሳዊ የሆኑ ጉዳዮች አያስጨንቁትም። አለባበሱም እንደነገሩ ነው። አንድ ጊዜ እንዲያውም ወደ አንድ ሆቴል ሊገባ ሲል የሆቴሉ ዘበኛ አመናጭቆ ይመልሰዋል፡፡ አያ ሙሌም ጠጋ ብሎ “ትናንትና በረባሶ አድርገህ ገብተህ ዛሬ በረባሶ ያደረገ ሰው ትንቃለህ” ሲል ተናገረው ይባላል።

> ‹‹የግጥም ስብስቦቹም ሆኑ የሙዚቃ ሥራዎቹ እያደር እንደ ወይን እየጣፈጡ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ቅኔዎቹን ከየትም አያመጣቸውም፡፡ ስለምን ልጻፍ እያለም አይጨነቅም፡፡ ሁሉንም ከሕይወቱ እየጨለፈ ይቀዳቸዋል፡፡ ከ30 ዓመታት በፊት የሰራቸው የሙዚቃ ግጥሞች ዛሬም ድረስ እንደ አዲስ ይደመጣሉ

ቀደም ሲል አያ ሙሌ ለኢህዴግ መንግሥት ትልቅ ባለውለታ ነበር። ወያኔ የደርግን መንግሥት ጥሎ ሲገባ እንዳገዛቸው ይነገራል። ከዚያ በኋላም ከባለሥልጣናቱ ጋር የቅርብ ወዳጅ ነበር። የእርሱን ግጥሞች መስማትም ያስደስታቸዋል። በተለያዩ ጊዜያትም ዝግጅቶች ሲኖሩ ከቤተመንግሥት ገብቶ ግጥሞቹን ያቀርብ ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን አያ ሙሌ ወደ ቢሯቸው ሄዶ የሰጡትን ሽጉጥ አስረክቦ ደመወዙንም ሳይቀበል ጥሎ ወደ ጎዳና ሕይወት ወጣ። በወቅቱም ታምራት ላይኔ መልዕክተኛ ልኮ እንዲመለስ ቢጠይቀው አያ ሙሌ ግን እንዲህ ነበር ያለው “አመሰግናለሁ መንገዴንም ለይቻለሁ” በሌላ ጊዜ ደግሞ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበረው በረከት ስምኦን ካለበት ጎዳና ድረስ መጥቶ ቢያንስ የ11 ዓመት ህጻን ልጅህ አታሳዝንህም ብሎ እንደለመነው ይነገራል፡፡

ከዚህ በኋላ የአያ ሙሌ ሕይወት እንደማንኛውም የጎዳና ልጅ ሆነ። እየዞረ ለምኖ ያመጣውን ምግብ መልሶ ለሌሎች የጎዳና ልጆች ይሰጣል። ከልክ ያለፈ ደግነቱ እዚህም ተከትሎት መጣ። በጎዳና ላይ እያለ ለስጋው የምትሆን ትንሽዬ ምግብ ካገኘ በቂው ነበር። ፈጽሞ ግን በኪሱ የሚያስቀምጣት ገንዘብ አይፈልግም። ገንዘብ እንዲሰጡትም አይለምንም። አያ ሙሌ ልክ የወፊቱን አይነት ኑሮ መኖር ጀመረ። ወፊቱ ሲል የራሱ ሕይወት ታይቶት ነበር። አደራ ልጄን አደራ ብሎ ሲጽፍም ልጁን ጥሏት እንደሚሄድ ተገልጦለት ነበር። እነዚህን ነገሮች ስንመለከት ባለቅኔው ነብይም ጭምር ነበር እንድንል ያደርገናል። አያ ሙሌ እንደዋዛ ጎዳና ላይ ወጥቶ ከባዘነ በኋላ ልጁን በአደራ ተቀብላ ስታሳድግ የነበረችው ስንዱ አበበ ነበረች። እርሱ ከጎዳና እንዲመለስ ጥረት ብታደርግም ሊሳካላት አልቻለም። አያ ሙሌ የሚጽፋቸው ግጥሞች የትም የማይገኙ ትልቅ ሀብት ቢሆኑም እርሱ ግን እየጻፈ ይተዋቸው ነበር። የእርሱን ግጥሞች ካሉበት ሁሉ እየሰበሰበች በመጽሃፍ መልክ ያሳተመችውም ስንዱ አበበ ናት።

የአያ ሙሌ የሕይወት ጀንበር እያዘቀዘቀች ስትመጣ ሌላ አስፈሪ ጭለማ ወደ እርሱ እየቀረበ እንደሆን ተረድቶ ነበር። በቀናት የሚቆጠር በጣም አጭር የምድር ቆይታ እንደቀረው ሲረዳ አሁንስ ማረፍ እፈልጋለሁ በማለት ልጁን ካገኛት በኋላ ከቤተክርስቲያን ደጅ ቆሞ ረዥም ጸሎት አደረገ። ከዚያም አዲስ አበባን ለቆ በመኪና ተሳፍሮ ወደ ዓለም ገና አመራ። እዚያም ከአንድ ሆቴል መኝታ ይዞ አደረ። ሲነጋ ግማሽ በድን ሆኖ ተገኘ። ነብሱ ግን አልወጣችም ነበር፡፡ ይዘውት በሚወጡበት ሰዓት ዘበኛው ይህንን አለ “ኧረ ይሄስ ነብይ ሳይሆን አይቀርም። ሌሊቱን ሙሉ ለጆሮ የሚከብዱ ነገሮችን ሲናገር ነው ያደረው” በማግስቱ ነሀሴ 28 ቀን 1996 ዓ/ም አረፈ፡፡ አያ ሙሌ ባለቅኔው ሙሉጌታ ተስፋዬ የእርሱ ሕይወት ቅኔ እንደሆነ ለእኛ ግን ዘመን የማይንዳቸው የቅኔ ሥራዎቹን ትቶልን ወደማይመለስበት ሄደ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## በኡጋንዳ ከአይኤስ ጋር ግንኙነት ያለው ታጣቂ ቡድን ሕጻናትን ጨምሮ 40 ሰዎችን ገደለ

በምዕራብ ኡጋንዳ ከጽንፈኛው እስላማዊ ቡድን እስላሚክ ስቴትስ ጋር ግንኙነት አለው የተባለ ታጣቂ ቡድን ሕጻናትን ጨምሮ 40 ሰዎችን ትምህርት ቤት ውስጥ ገደለ። ማፖውድዌ በተባለ አካባቢ በሚገኘው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ በተፈጸመው ጥቃት አብዛኛው ሟች ሕጻናት መሆናቸው የተነገረ ሲሆን፤ ከሟቾቹ በተጨማሪ 8 ሰዎች ለሕይወት አስጊ የሆነ ጉዳት ደርሶባቸዋል ተብሏል።

በትምህርት ቤቱ ማደሪያ ክፍል ውስጥ የነበሩ ወንድ ልጆች ከሟቾቹ መካከል ይገኛሉ። አርብ ዕለት ለተፈጸመው ጥቃት መቀመጫውን ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ያደረገው አላይድ ዴሞክራቲክ ፎርስ (ኤዲኤፍ) ተጠያቂ ተደርጓል። አርብ እኩለ ሌሊት አካባቢ ጥቃቱ የደረሰበት ትምህርት ቤት እዛው ነዋሪ የሆኑ 60 ተማሪዎችን ያስተምራል።

የኡጋንዳ ፖሊስ ቃል አቀባይ ፍሬድ ኢናንጋ ታጣቂ ቡድኑ አባላት የተማሪዎች መኖሪያ ቤቶችን በእሳት ካጋዩ በኋላ ምግብ ዘርፈዋል ብለዋል። አንዳንዶቹ ልጆች ተቃጥለው አልያም በስለት አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ተወግተው ተገድለዋል። በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ የነበሩ አብዛኞቹ ሴቶች የሆኑ ልጆች በቡድኑ ተጠልፈው መወሰዳቸው ተነግሯል።

የጥቃቱ ሰለባዎች እድሜን በተመለከተ የታወቀ ነገር የለም። የተወሰኑት አስከሬኖች ክፉኛ በመቃጠላቸው ማንነታቸውን ለመለየት የዘረ መል ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል። ጥቃት ፈጻሚዎቹ ተማሪዎቹ የሚተኙባቸውን ፍራሾች ያቃጠሉ ሲሆን፤ በአካባቢውም ቦምቦችን አፈንድተዋል። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ ክፍሎች በእሳት ሲቃጠሉ የሚያሳዩ ፎቶዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ታይተዋል።



ከተማሪዎቹ በተጨማሪ የአካባቢውን ማህበረሰብ አባላት ጨምሮ በጥቃቱ ሳይገደሉ አይቀርም ተብሏል። እስካሁን ድረስ 40 ሰዎች መሞታቸው ይረጋገጥ እንጂ እያንዳንዱ ተማሪ ተቆጥሮ ስላላለቀ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ሊጨምር ይችላል የሚል ስጋት አለ።

ጥቃቱን ተከትሎ የኤዲኤፍ ሽምቅ ተዋጊዎች ወደ ዴሞክራቲክ ኮንጎ የሸሹ ሲሆን፤ የኡጋንዳ ጦር ታጣቂዎቹን እየተከተለ ነው ተብሏል። የኤዲኤፍ ሚሊሻ አባላት ሩዋንዳ እና ኡጋንዳን በሚያዋስነው የዴሞክራቲክ ኮንጎ በአፍሪካ ትልቁ ቪሩንጋ ፓርክ ውስጥ በመሸሸግ ይታወቃሉ።

"ጦራችን ጠላትን ለማጥፋት እና የተጠለፉትን ለማስጣል እግር በግር እየተከተላቸው ነው" በማለት የኡጋንዳ ጦር ቃል አቀባይ ፌሊክስ ኩላዩግዬ በትዊተር ገጻቸው ላይ ጽፈዋል።የኡጋንዳ ጦር ሄሊኮፍተሮችን ጨምሮ ወደ ስፍራው በማሰማራት የታጣቂ ቡድን አባላቱን እያሳደደ ነው ተብሏል። ከዚህ ቀደም ኡጋንዳ እና ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ይህን ታጣቂ ቡድን ለማጥፋት የጋራ ዘመቻዎችን ሲያካሂዱ ነበር።

የታጣቂ ቡድኑ አባላት አርብ ዕለት ጥቃቱን ከማድረሳቸው በፊት ለሁለት ቀናት በኮንጎ እና ኡጋንዳ ድንበር አቅራቢያ ይገኙ እንደነበር የኡጋንዳ ደኅንነት ቢሮ መረጃው ነበረው ተብሏል።ይህ ጥቃት የተፈጸመው ባለፈው ሳምንት የኤዲኤፍ ሚሊሻ አባላት ናቸው የተባሉ ታጣቂዎች በአንዲት የኮንጎ መንደር ላይ ጥቃት ፈጽመው ከ100 ያላነሱ ሰዎች ወደ ኡጋንዳ ከተፈናቀሉ በኋላ ነው።

ጥቃቱ የተፈጸመበት ትምህርት ቤት ከኮንጎ ድንበር ሁለት ኪሎ ሜትር ብቻ ርቆ የሚገኝ ሲሆን፤ በኡጋንዳ ትምህርት ቤት ላይ ጥቃት ሲሰነዘር ይህ ከ25 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። እአአ 1998 ላይ ይህ ታጣቂ ቡድን እንዲሁ ትምህርት ቤት ላይ ባደረሰው ጥቃት 80 ተማሪዎች በመኖሪያ ክፍሎቻቸው ውስጥ በእሳት ተቃጥለው ሞተው ነበር። ከሟቾቹ በተጨማሪ 100 ተማሪዎች ተጠልፈው ተወስደዋል።

እራሱን አላይድ ዴሞክራቲክ ፎርስ ብሎ የሚጠረው ቡድን የፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቪኒ መንግሥት ሙስሊሞችን ይጨቁናል በሚል እአአ 1990ዎቹ በምስራቅ ኡጋንዳ ነበር ተመስርቶ ብረት ያነሳው። መንግሥታዊ አሃዞች ከአጠቃላይ የኡጋንዳ ሕዝብ የሙስሊም ማህበረሰቡ ቁጥር 14 በመቶ ነው ይበል እንጂ የኡጋንዳ የእስላምና ጠቅላይ ምክር ቤት አሃዙን ወደ 35 በመቶ ከፍ ያደርገዋል።

አንዳንድ የኡጋንዳ ሙስሊሞች በሃይማኖታችን ምክንያት በማህበራዊ ሕይወት፣ በትምህርት እና በሥራ ቦታዎች ላይ መገለል ይደርስብናል ይላሉ። እአአ 2001 ላይ ኤዲኤፍ በኡጋንዳ መንግሥት ከፍተኛ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ ዋና መቀመጫውን ወደ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ኪቩ ግዛት አዘዋውሮ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የትጥቅ ትግል እያደረገ ይገኛል።የዚህ ቡድን መስራች ጃሚል ማኩሉ እአአ 2015 ላይ በታንዛኒያ በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ለኡጋንዳ ተላልፎ ተሰጥቶ በእስር ላይ እንደሚገኝ ጠቅሶ የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት





# የረጅም ርቀት ንጉሡ ረጅም የአትሌቲክስ ሕይወት

ዓስማየሁ ግዛው

ውድድር ከጀመረ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል፤ ዛሬም ድረስ ግን ሳይታክት በታላላቅ የውድድር መድረኮች መሮጡን ቀጥሏል፡፡ በዚህም ጎልሶ እንካን የትልልቅ መገናኛ ብዙሃን ትኩረት ሳይስብ ቀርቶ አያውቅም። የረጅም ርቀት፣ የመምና አገር አቋራጭ ውድድሮች ንጉሡ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ፣ ባለፈው ማክሰኞ የ41ኛ ዓመት ልደት ሻማውን መለኮሱን ተከትሎም መላው ዓለም የእንኳን አደረሰህ መልእክቱን አዥጎድጉዶለታል። ለቁጥር ከሚያታክቱ የታላላቅ መድረኮች ስኬቱ ባሻገር ለማመን በሚከብዱ በርካታ ክብረወሰኖች ደምቆ ረጅሙን የአትሌቲክስ ሕይወት እያገባደደ ይገኛል፡፡

የብዙዎች ብርታትና ጥንካሬ ተምሳሌት በመሆን አንበሳው አትሌት ቀነኒሳ በስፖርቱ ዓለም ታሪክ ውስጥ በጉልህ ስፍራ ይቀመጣል፡፡ በአትሌቲክስ ስፖርት ታሪክ የታየ የምንጊዜም ምርጡ አትሌት ነው። «አቦሸማኔው» የተወለደው እአአ ሰኔ 13 ቀን 1982 ነው፡፡ የትውልዱ ስፍራውም የአትሌቶች መፍለቂያ በሆነችው በቆጂ ነው፡፡ የአትሌቲክስ ሕይወቱን የጀመረውም ገና በለጋ እድሜው ነበር። ሲሮጥ ያምርበታል፣ አትሌቲክስን በእውቀት ጭምር ነው የሚወዳደርበት፡፡ አስደናቂ ጽናትና ፍጥነት መለያው ነው፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ከምን ጊዜውም ምርጥ የረጅም ርቀት ሯጮች ግንባር ቀደም ያሰኙት ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፡፡ በኦሊምፒክ፣ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናና በዓለም አገር አቋራጭ ከፍተኛ ክብረወሰን አስመዝግቧል፡፡

ቀነኒሳ በአገር አቋራጭ፣ በመም (ትራክ) እና በጎዳና ውድድሮች በርካታ ድሎቹ አገሩን አኩርቷል። በተለያዩ ውድድሮች ለኢትዮጵያ 26 የወርቅ ሜዳሊያዎችን አበርክቷል፡፡ የ5ሺ እና የ10ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰኖችን ከ15 ዓመታት በላይ ተቆጣጥሮ ቆይቷል። የማራቶንን ሁለተኛ ፈጣን ሰዓት በ2፡01፡41 ሰዓት ያስመዘገበው ታላቅ አትሌት ዛሬም በርቀቱ ቀዳሚውን ሰዓት ለማስመዝገብ ያለው ፍላጎት አልከሰመም፡፡ በሩጫ ዘመኑ ከ120 በላይ ውድድሮችን አሸንፏል፡፡

ቀነኒሳ በኦሊምፒክ መድረክ ሶስት አስደናቂ የወርቅ እና አንድ የብር ሜዳሊያን የግሉ አድርጓል። በዓለም አገር አቋራጭ 16 የወርቅ እና አንድ የብር ሜዳሊያ፣ በዓለም ቻምፒዮና አምስት የወርቅ እና አንድ የነሃስ ሜዳሊያ፣ በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና 1 ወርቅ በአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሁለት የወርቅ ሜዳሊያ፣ በመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን አግኝቷል።

በ2004 የአቴንስ ኦሊምፒክ በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ እና በ5ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ፤ በ2008 የቤጂንግ ኦሊምፒክ በ5ሺ እና 10ሺሜትር ድርብ ድልን የተጎናፀፈበት አጋጣሚ የማይረሳ ወርቃማ ታሪኩ ነው። ቀነኒሳ ከ2003 ጀምሮ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለአራት ጊዜ የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮን መሆን ችሏል። በመድረኩ በአጠቃላይ 5 የወርቅ ሜዳለያና 1 የነሐስ ሜዳለያ ባለቤትም ነው፡፡

ቀነኒሳ በትራክ ውድድር ካስመዘገበው አስደናቂ ስኬት በተጨማሪ በማራቶን ሩጫም የላቀ ውጤት አስመዝግቧል። እ.ኤ.አ. በ2014ቱ የፓሪስ ማራቶን ውድድር ስድስተኛውን የማራቶን ፈጣን ሰዓት በ2፡05፡04 አሸንፏል። እ.ኤ.አ. መስከረም 25 2016 የበርሊን ማራቶንን 2፡03፡03 በሆነ አዲስ የግል ምርጥ ሰዓት በማስመዝገብም በወቅቱ የምንጊዜውም የማራቶን ሶስተኛው ፈጣን አትሌት ለመሆን በቅቷል፡፡ እአአ መስከረመ 29 ቀን 2019 የበርሊን ማራቶንን በ2፡01፡41 በሆነ ጊዜ በድጋሚ አሸንፏል፣ ይህም በ2018 የበርሊን ማራቶን ከተመዘገበው የኤሊዩድ ኪፕቾጌ የዓለም ክብረወሰን በ2 ሰከንድ የዘገየ ነበር።

ዓለም የቀነኒሳን 41ኛ ዓመት የልደት በዓል ሲያከብር ኢትዮጵያዊው የረዥም ርቀት ሯጭ በአትሌቲክሱ ዓለም ያሳረፈውን አሻራ እያሰበ ነው፡፡ የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌት፣ የትራክና የጎዳና ውድድሮች ምርጥ አትሌትና የኢትዮጵያ የዓመቱ በጎ ሰው የሚሉ ክብሮችን መቀዳጀት የቻለውን ታላቅ አትሌት ወደፊትም በተለይ የማራቶን ክብረሰወሰን ለመስበር እየሰራ ነው። እኛም 41ኛ ዓመት የልደት በዓሉ አስመልክቶ እንኳን ተወለድክ ብለን ከብዙ በጥቂቱ የአትሌቲክስ ስኬቶቹን ለማስታወስ ወደናል፡፡



የረጅም ርቀት የምንጊዜም ምርጡ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ 41ኛ ዓመቱን አከበሯል፣




# ሰኔ አምስትን ለሕጻናት

ጽጌረዳ ጫንያለው

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? በጣም ጥሩ ነው እንደምትሉ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም ጎበዝና ቤተሰቡን የምትሰሙ ልጆች እንደሆናችሁ አውቃለሁ። ይህንን የሚያደርግ ልጅ ደግሞ በትምህርቱ ውጤታማ እንደሚሆን ማወቅ አለባችሁ፡፡

ልጆች ለዛሬ ይዤላችሁ የቀረብኩት ሃሳብ የምታውቁት ቢሆንም በድጋሚ ማንሳትና ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ይዤላችሁ የቀረብኩት ጉዳይ ጠቃሚ ነው፣ ምንድነው እሱ? ካላችሁ ስለሰኔ 5 ነው የምነግራችሁ፡፡ እንደምታውቁት ሰኔ አምስት የዓለም ፀረ-ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ቀን ነው፡፡ ለምን ይከበራል ካላችሁ ደግሞ ቀጣዮቹን ምክንያቶች አንብቡ፡፡

ልጆች ቀኑ የሚከበርበት ምክንያት አንድ እና አንድ ነው፡፡ ልጆች ከአቅማቸው በላይ ሥራ እንዳይሰሩ ማድረግ፤ ቤተሰባቸው ያላግባብ በስራ ጠምደው ለጭንቀት እንደይዳረጉ መከላከል፤ ልጆችም መብትና ግዴታቸውን አውቀው ቤተሰባቸውን እንዲያገለግሉ ማስቻል ነው፡፡ ቀኑ ሲታሰብ በሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ሁሉም ሰው ማድረግ ያለበትን እንዲያውቅ ይሆናል፡፡ ስለዚህም የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ይቀራል፡፡

ልጆች ሕጻናት የጉልበት ብዝበዛ ደርሶባቸዋል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? እስቲ ትንሽ ላብራራላችሁ፣ ሕፃናት በጉልበት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ሲባል በየሳምንቱ ለ21 ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ በቤት ውስጥ ወይም በሌላ የሥራ መስክ ላይ ተጠምደው ውለዋል ማለት ነው፡፡ ይህ የጉልበት ብዝበዛ ደግሞ ሕጻናት ላይ አርፏል የሚባለው የእድሜ ክልሉ ከአምስት እስከ 14 ዓመት ላይ ሲሆን ነው፡፡

የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ሊፈጠር የሚችልባቸው ምክንያቶች በርካታ ናቸው። ዋነኛው ግን የኢኮኖሚ ችግር እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም የኢኮኖሚ መዛባት እና የብሔራዊ በጀቶች መቀነስ የዓለም የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በእጅጉ ከጨመሩት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ የመከሰቻ አጋጣሚው ደግሞ በተለይም የትምህርት ቤቶች መዘጋት የሥራ ማጣት፣ የኑሮ ሁኔታ እና የማኅበራዊ ደህንነት እና የኢኮኖሚ እጦት ናቸው፡፡ የህዝብ ብዛት መጨመር፣ ተደጋጋሚ ቀውሶች፣ ከፍተኛ ድህነትም እንዲሁ ችግሩን ከሚፈጥሩት መካከል ናቸው፡፡ ለመሆኑ ይህና ይህን መሰል ምክንያቶች ምን ያህል ሕጻናትን ጎድተዋል ካላችሁ ካነበብኩት ያገኘሁትን መረጃ ላካፍላችሁ፡፡

በዓለም ዙሪያ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በቁጥር ወደ 160 ሚሊዮን ከፍ እንዳለ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባወጣው መግለጫው ያስረዳል፡፡ ይህ ቁጥር ደግሞ በየዓመቱ ከፍተኛ ጭማሪ ያሳያል፡፡ ይህ ቁጥር በተለይም በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ተጽዕኖዎች ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሌሎች ሕጻናት ወደ አስገዳጅ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ የመግባት አደጋ ተጋርጦባቸው እንደነበር ያወሳል።

የዓለም ፀረ-ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ቀንን አስመልክቶ ይኸው ድርጅት ከሁለት ዓመት በፊት ባወጣው መረጃ እንዳስቀመጠው፤ የህጻናትን ጉልበት ብዝበዛ ለማስቆም የተጀመረው ሥራ ግቡን ሳይመታ በመቅረቱ የተነሳ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አስገራሚ በሆነ መልኩ ቀደም ሲል እያሽቆለቆለ የነበረው አሃዝ በመቀልበስ ከፍተኛ በሆነ ቁጥር መጨመር አሳይቷል፡፡ እኤአ በ2000 እና በ2016 ባሉት ዓመታት መካከል 94 ሚሊዮን ሕጻናት ለአስገዳጅ የጉልበት ብዝበዛ ተዳርገዋል።

በልጆች የጉልበት ሥራ ላይ ያሉ ሕፃናት ረዘም ላለ ሰዓት መሥራት ወይም በከፋ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እንዲሰሩ ይገደዳሉ፡፡ ብዙዎች ደግሞ በተጎጂዎች መካከል ሥራ በማጣት እና ገቢ በማጣት ወደ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች ሊገቡ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በወንድ ልጆች ላይ ይከፋል፡፡ በተለይም በገጠር አካባቢዎች የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በጣም የተለመደ ነው።

ይህ ማለት ከከተማ ሕፃናት ጋር ሲነፃፀር በገጠር አካባቢዎች የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ (13 ነጥብ 9 በመቶ) ሲሆን፤ በከተማ ከሚገኘው (4 ነጥብ 7 በመቶ) አሃዝ ይሆናል። ስለዚህ አሃዙ በሦስት እጥፍ ይበልጣል። በህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዋነኛው እና ትልቁን ድርሻ የሚወስደው በቤተሰብ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ሲሆን፤ ግብርናው በስፋት ይጠቀሳል።

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በተደጋጋሚ ሕጻናቱ ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን የጉልበት ብዝበዛ ሁሉም ሊታገለው ይገባል፡፡ ምን በመስራት ካላችሁ የመጀመሪያ የሚሆነው ግንዛቤ በመፍጠር አገራት ገቢያቸውን ከፍ የሚያደርጉበትን መንገድ መቀየስ፤ ልጆች ወደነበሩበት ትምህርት ቤት እንዲመለሱ የማህበራዊ ጥበቃ መርሃ ግብሮች ማስፋት፤ ሕጻናት ለመብታቸው እንዲሟገቱ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም መብታችሁን አውቃችሁ የሕጻናት ጸረ ጉልበት ብዝበዛ ትግል ልታደርጉ ይገባችኋል በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን።

ሰላም!!